አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ
BIIROO BARNOOTA BULCHINSA MAGAALAA FINFINNEE
ADDIS ABABA CITY ADMINISTRATION EDUCATION BUREAU

# የክወናና የዕይታ

## ጥበባት ትምህርት



2ኛ ክፍል

## የተማሪ መማሪያ

2ኛ ክፍል



# የሁለተኛ ክፍል
# የክወናና የዕይታ ጥበባት ትምህርት

## የተማሪ መማሪያ

ጸሐፊያን፡- ረድኤት ሙሉጌታ
በኃይሉ ዘለቀ
ሳራ መንግስቱ

ገምጋሚዎች፡- እየሩሳሌም በዳኔ
ማርቆስ ወልደሐና
ሰሎሞን ኃይለማርያም

አስተባባሪ፡- ጌታቸው ታለማ አጥናፉ

ግራፊክ ዲዛይን፡- እንጦጦ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ

2014

መብቱ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ነው ©

# ምስጋና

ይህን የትምህርት መጽሐፍ ከዝግጅት ጀምሮ በውጤት እንዲጠናቀቅ፣ የካበተ ልምዳቸውን በማካፈል፣በፓናል ውይይት ሃሳብ በማፍለቅና በማቅረብ፣ በከተማችን በሚያስተምሩ መምህራን እንዲዘጋጅ በማድረግ፣ አስፈላጊውን በጀት በማስፈቀድ እንዲሁም በጥብቅ ዲስፕሊን እንዲመራ በማድረጋቸው ላደረጉት ከፍተኛ ድጋፍ የትምህርት ቢሮ ኃላፊ አቶ ዘላለም ሙላቱ የላቀ ምስጋና ይገባቸዋል፡፡

ለሥራችን መሳካት ሁልጊዜ አብረውን በመሆን፣ በሚያጋጥሙ ችግሮች መፍትሄ በመስጠት፣ የአፈጻጸም ሂደቱን በመከታተል፣ በመገምገም እንዲሁም የዝግጅቱ ስራ ቁልፍ ስራ መሆኑን ተረድተው ትኩረት በመስጠት ከጎናችን ለነበሩ የትምህርት ቢሮ የማኔጅመንት አባላት የስርዓተ ትምህርት ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ አድማሱ ደቻሳ ፣ የትምህርት ቴክኖሎጂ ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ዳኛው፣ ገብሩ የመምህራን ልማት ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ሳምሶን መለሰ፣ የትምህርት ቢሮ ኃላፊ አማካሪ ወ/ሮ አበበች ነጋሽ፣ የትምህርት ቢሮ ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ ሲሳይ እንዳለ፣ የቴክኒክ አማካሪ አቶ ደስታ መርሻ ላበረከቱት አስተዋጽኦ ምስጋና ይገባቸዋል፡፡

በመጨረሻም መጽሐፉ ተጀምሮ እስከሚጠናቀቅ ድረስ የትምህርት ቤት ርዕሳነ መምህራን ለስራው ልዩ ትኩረት በመስጠት አዘጋጅ መምህራንን ስለላካችሁልንና የሞራል ድጋፍ ስላደረጋችሁም ምስጋናችን እናቀርባለን፡፡

## ማውጫ

ርዕስ ገጽ

ምዕራፍ አንድ ጥበባዊ ግንዛቤ....1
መግቢያ....1
1.1 የሙዚቃ ኖታዎች....4
1. መሉ የድምፅ ኖታ....5
2. ግማሽ የድምፅ ኖታ....7
1.2 ነፃ እንቅስቃሴዎች (ውዝዋዜ)....10
ነፃ እንቅስቃሴ ማለት ምን ማለት ነው?....10
1.3. ቀላል የትወና ጨዋታዎች....13
1.4 ፎቶዎችን ማጤን....16
1.5 በየእለቱ የሚለማመዷቸው ምስሎች....27
ማጠቃለያ....36
ምዕራፍ ሁለት፡- ፈጠራን መግለፅ....37
2.1 የሙዚቃ ኖታዎች....38
2.2 ነፃ እንቃስቃሴዎች/ ውዝዋዜዋች....44
2.3 የትወና ጨዋታዎች....47
2.4 በመስመር መሞነጫጨርና መስመር መሳል....52
2.4.1 በመስመር መሞነጫጨር....52
2.4.2 መስመር መሳል....54
ማጠቃለያ፡-....60
ምዕራፍ ሶስት፡- ታሪካዊ እና ባህላዊ አውዶች....62
3.ባህላዊ እይታ....62
3.1 አገራዊ ሙዚቃ....62
አገራዊ ሙዚቃ እና ገፅታቸው....63
3.2 የአገራዊ ውዝዋዜ ባህላዊ እይታ....68
3.3 የድራማ እና ታዋቂ ተረቶች ባህላዊ እይታ....71
1 ተረቶች....72
2 እንቆቅልሾች....75
3.4 የቀለም ባህላዊ ገፅታ....77
3.4.1 የቀለም ጅማሬ በኢትዮጵያ....78
3.4.2 የሰንደቅ ዓለማ ትርጉም....81
ማጠቃለያ....83

ምዕራፍ 4 ሥነ-ውበታዊ እሴት (ዋጋ) ....................................85
መግቢያ..............................................................................85
4.1 የሙዚቃ ክዋኒዎችን ማድነቅ..........................................87
4.2 የውዝዋዜ ክዋኒያንን ማድነቅ..........................................91
4.3 ተውኔት ተጫዋቾችን ማድነቅ..........................................87
4.4 የእይታ ጥበብ ክዋኒዎችን ማድነቅ....................................99
ማጠቃለያ..........................................................................103
ምዕራፍ አምስት፡- ጥመርታ ዝምድናና ትግበራ..................................106
5.1 የሙዚቃ ተግባራት.......................................................107
5.1.1 ሙዚቃ ለሌሎች ትምህርቶች ያለው አስተዋጽኦ................110
5.1.2 ውዝዋዜ ለሌሎች የትምህርት አይነቶች ያለው አስተዋፅኦ.........................................................111
5.3.3 ቴቲያትር ሌሎች የትምህርት አይነቶች ያለው አስተዋፅኦ...112
5.3.4 ዕይታ ጥበብን መማራቸው ለሌሎች ትምህርት ዓይነቶች ያለውን አስተዋጽኦ..................................................116
5.2 በክወና እና በዕይታ ጥበባት መካከል ያለውን ዝምድና መለየት..........................................................120
ማጠቃለያ.......................................................................122

# ምዕራፍ 1

## ጥበባዊ ግንዛቤ

### መግቢያ

የክወና የእይታ ጥበባት በሰው ልጆች የዕለተ ህይወት ተዕለት

ውስጥ ከፍተኛ ሚና አለው ::

የስነጥበብ ዘርፍ ከዕለተ ተዕለት ህይወት ጋር ይገናኛል::

በትምህርት አለም ውስጥም ያለው አስተዋጽኦ ቀላል ግምት

የሚሰጠው አይደለም::

ለሥነ ጥበብ ዘርፍ ትኩረትን መስጠት ተገቢ ነው:: ከየትኛውም

የትምህርት አይነት ጎን ለጎን ማስኬድ ያስፈልጋል::

ተማሪዎች ከልጅነት እድሜአቸው አንስቶ በሙያው ላይ

የሚኖራቸውን ግንዛቤ እና እውቀት መዳበር አለበት::

ምክንያቱም ሙያውን ከማሳደግም ባለፈ በሙያው የሰለጠኑ

የህብረተሰብ ክፍሎችን ቁጥር ከፍ ያደርገዋል::

## ከዚህ ክፍለ ትምህርት በኋላ የሚጠበቅ የመማር ውጤት

ከዚህ የክፍል ደረጃ በኋላ የሚከተሉትን ትችላላችሁ፡-

- ቀላል የትወና ጫዋታዎችን ትጫወታላችሁ፡፡
- የሙዚቃ ኖታዎች ከሙሉ ኖታ እስከ ግማሽ ኖታ ከነእረፍት ኖታቸው ትለያላችሁ፡፡
- ነፃ ውዜዋዜ ትለያላችሁ፡፡
- ተመልክታችሁ ያስተዋላችኋቸውን ቀላል ሥዕሎችንና ፍቶግራፎችን ታስረዳላችሁ፡፡ የሞነጫጨራችሁትንና በመስመር የሳላቹአቸውን ሥዕሎች ታሳያላችሁ፡፡
- በታዋቂ ታሪኮች ላይ ተመስርታችሁ የተዘጋጁ ድራማዎችን፣ ሙዚቃዎችንና ውዜዋዛዎችን ትስራላችሁ፡፡
- በአካበቢያቸው የሚገኙትን ቀለማት ትለያላችሁ፡፡
- ክ.እ.ጥ.ን መማራችሁ ለሌሎች ትምህርት ዓይነቶች ያለውን አስተዋፅኦ ትገልጻላችሁ

## መለየት

ተማሪዎች በተለያዩ አጋጣሚዎች ከልጅነት ዘመናቸው ጀምሮ ለማንኛውም የጥበብ ዘርፍ ፍቅር እንዳላቸው የሚታወቅ ነው። ሆኖም የሚወዱትን እያወቁት ቢመጡ የበለጠ ግንዛቤን ያዳብራሉ።

በዚህ ምዕራፍም ስለሙዚቃ ኖታዎች ግንዛቤን የገኛሉ። ቀላል ትወናዎችን ፎቶገራፎችን እንዲሁም ምስሎችን እየተለማመዱ መረዳትና መለየት ይችላሉ።

### ከዚህ ምእራፍ የሚጠበቅ የመማር ውጤት

- የእያንዳንዱን የሙዚቃ ኖታ ታውቃላችሁ
- ቀላል እንቅስቃሴዎችን ትከናውናላችሁ
- ቀላል የትወና ጨዋታዎችን ትጫወታላችሁ
- ፎቶገራፎችን እና ምስሎችን በአግባቡ ትለያላችሁ

## 1.1 የሙዚቃ ኖታዎች

### ከዚህ ርእስ መጠናቀቅ

- የሙዚቃ ኖታዎችን ትለያላችሁ፡፡
- የሙዚቃ ኖታ አቆጣጠር ዘዴ ትረዳላችሁ፡፡

## መግቢያ

### የሙዚቃ ኖታ ማለት ምንድን ነው?

ኖታ የድምጽ ጊዜንና የዕረፍት ጊዜን የሚያመለክቱ ምልክቶችን በ አንድ ላይ የምንጠራበት ቃል ነው፡፡ ኖታ በሁለት ይከፈላል፡፡እነሱም የድምፅ ኖታ እናየእረፍት ኖታ ናቸው፡፡የሙዚቃ ኖታ ሙዚቃ ውስጥ ያለውን ጊዜ እና ምትየምንገልፅበት ነው፡፡

### የሙዚቃ ኖታዎች

በዚህ ክፍለ ትምህርት ላይ ሁለቱን የኖታ አይነቶች ትማራላችሁ፡፡

እነሱም የድምፅ ኖታ እና የእረፍት ኖታ ናቸው፡፡

1 ሙሉ የድምፅ ኖታ (whole note)



2 ግማሽ የድምፅ ኖታ (haf note)



## 1 ሙሉ የድምፅ ኖታ



ሙሉ ኖታ የምንለው ቅርፁ ከእንቁላል ጋር ተመሳሳይነት ያለው ነው። ኖታውም አራት ምት የጊዜ ቆይታ አለው።

ሙሉ ኖታ በሶስት አይነት መንገድ ይገለጻል።

1. በቁጥር 2.በፊደል እና 3.በሥዕል

## ሙሉ የድምፅ ኖታ በቁጥር

ሙሉ ኖታ ሲቆጠር አንድ፤ሁለት፣ሶስት፣አራት (1 2 3 4) እያልን በእግር ጣት ይቆጠራል።

## ሙሉ የድምፅ ኖታ በፊደል

ሙሉ ኖታ በቁጥር እንደቆጠርነው በአንድ ፊደል ደግሞ ታ_____ እያልን በአፋችን ድምፃችን ሳናቆራርጥ እንቆጥረዋለን

## ሙሉ የድምፅ ኖታ በሥዕል

ሙሉ የድምፅ ኖታ በስዕል መንገድ የሚገለፀው የእንግሊዝኛው ፊደል V የሚመስል ቅርፅ አራት ጊዜ ተቀጣጥሎ ሲታይ ነው፡፡ መምህራችን በስዕል ሲያሳዩ በትኩረት ተከታተሉ፡፡



## የሙዚቃ እረፍት ኖታ

➢ በሁለተኛ ክፍል ሁለቱን የሙዚቃ እረፍት ኖታዎችን እንማራለን፡፡

የሙዚቃ እረፍት ኖታ ማለት ሙዚቃ ድምፅ እንዳላቸው ሁሉ የእረፍት ወይም የዝምታ ጊዜ እንዳለው የሚያሳይ ኖታ ነው፡፡በዚህ ክፍለ ትምህርት ሁለቱን እንማራለን፡፡ እነሱም ፡- ሙሉ እረፍት ኖታ እና ግማሽ የእረፍት ኖታ ናቸው፡፡

ሙሉ የእረፍት ኖታ 

ግማሽ የእረፍት ኖታ 

## ሙሉ እረፍት ኖታ

ሙሉ የእረፍት ልክ እንደ ሙሉ ኖታ በቁጥር አራት ምት አለው፡፡ ኖታ ቅርፁ ከተደፋ ባርኔጣ ኮፍያ ቅርፅ ጋር የሚመሳሰል ሲሆን አራት ምት የዝምታ የጊዜ ቆይታ አለው ፡፡

## ➢ ሙሉ እረፍት ኖታ በቁጥር

ኖታውን በምንቆጥርበት ጊዜ በውስጣችን ምንም ዓይነት ድምፅ ሳናሰማ አራት የዝምታ ጊዜ አንድ፤ሁለት፤ሶስት፤አራት 1 2 3 4 እያልን በውስጣችን እንቆጥራለን፡፡

## ➢ ሙሉ እረፍት ኖታ በስእል

ከዚህ በፊት በምናውቀው የእንግሊዝኛ ፊደል V በሚመስል ቅርፅ ተቀጣጥሎ አራት የዝምታን ጊዜ ይለካልናል፡፡



**መልመጃ 1፡-**

ሙሉ የድምፅ ኖታን እና ሙሉ የእረፍት ኖታን በደብተራቹ ላይ ጻፉ።

## 2 ግማሽ የድምፅ ኖታ

ይህ የኖታ አይነቱ ልክ እንደ ሙሉ የድምፅ ኖታ የክብ አይነት ቅርፅ ያለው ሲሆን የሚለየውም ከጐን በኩል ወደ ላይ ዘንግ መኖሩ ነው፡፡ሁለት ምት የያዘ ቆይታም አለው፡፡

ግማሽ ኖታ ልክ እንደ ሙሉ ኖታ በሶስት አይነት መንገድ ይገለፃል እነርሱም በቁጥር፣ በፊደል እና በምስል ናቸው፡፡

- **ግማሽ የድምፅ ኖታ በቁጥር፡-**

ይህ ኖታ አንድ፣ ሁለት (1 2) እየተባለ በሁለት ምት የቁጥር ቆይታ ይገለፃል፡፡

- **ግማሽ የድምፅ ኖታ በፊደል፡**

ግማሽ የድምፅ ኖታ በአንድ አማርኛ ፊደል ይገለፃል፡፡ ይኸውም ታ ____ እያልን ነው፡፡ ስነቆጥር ምንም አይነት ድምፅ መቆራረጥ መኖር የለበትም ፡፡መምህራችን በምሳሌ ሲያስረዱ ማዳመጥ

- **ግማሽ የድምፅ ኖታ በሥዕል**

ይህ ኖታ በስዕላዊ መንገድ ሲገለፅ ከዚህ በፊት በምናውቀው ሁለት የእንግሊዝኛ ፊደል V ሲቀጣጠል የሚሰጠው ቅርፅ ነው፡



## ግማሽ እረፍት ኖታ

ይህ ኖታ ከግማሽ የድምፅ ኖታ ጋር በቁጥር እኩል ነው፡፡ ስለዚህም በውስጡ ሁለት የዝምታ ጊዜ አለው የግማሽ እረፍት ምልክት ቅርፁ ባርኔጣ ይመስላል፡፡

➢ **ግማሽ የእረፍት ኖታ በቁጥር**

ግማሽ የእረፍት ኖታ በቁጥር ሲገለፅ አንድ፣ ሁለት (1,2) እየተባለ ድምፃችንን ሳናሰማ እንቆጥራለን ። መምህራችን ሲያስረዱ በደንብ መከታተል ይኖርባቹሃል።

➢ **ግማሽ የእረፍት ኖታ በስእል**

ከዚህ በፊት በምናውቀው ሁለት የእንግሊዘኛ ፊደልV ተቀጣጥሎ የሚሰጡት ቅርፅ ነው።  ማዳመጥ። በምሳሌው መሰረትም መለሳቹ መለማመድ።

➢ ግማሽ የድምፅ ኖታ በሥዕል

ይህ ኖታ በስዕላዊ መንገድ ሲገለፅ ከዚህ በፊት በምናውቀው ሁለት የእንግሊዝኛ ፊደል V ሲቀጣጠል የሚሰጠው ቅርፅ ነው፡ 

መልመጃ 3 ፡-

መምህራችሁ የፃፉትን ኖታዎጋ ደጋግማችሁ በደብተራችሁ በደብተራችሁ ላይ ፃፉ

የድምፅ ኖታ እና የእረፍት ኖታ ማጠቃለያ መልመጃዎች

1. ኖታ ማለት ምን ማለት ነው።
2. ኖታ ለምን እንደሚጠቅም ግለፁ
3. ሙሉ የድምፅ ኖታ ስንት ምት አለው።
4. ግማሽ የድምፅ ኖታ በስዕል እና በቁጥር አሳዩ

5. ሙሉ የድምፅ ኖታ እና ግማሽ የድምፅ ኖታ
ሌዩነታቸውን እና አንድነታቸውን ግለፁ?
6. እረፍት ኖታ ምልክትን የምንጠቀመው በምን ጊዜ ነው።
7. ሙሉ የድምፅ ኖታ እና ግማሽ እረፍት ኖታ ልዩነታቸውን
እና አንድነታቸውን ግለፁ።

## 1.2 ነፃ እንቅስቃሴ እና ውዝዋዜ



### ከዚህ ንዑስ ርዕስ በኋላ የሚጠበቅ የመማር ውጤት

- ለውዝዋዜ ያለችሁ ፍቅር ያድጋል
- የውዝዋዜ ልምምድ ድፍረት ታገኛላችሁ
- ውዝዋዜዎችን በፍላጎታችሁ ትለምዳላችሁ
- የውዝዋዜ ክህሎት ታዳብራላችሁ

### መግቢያ

**ነፃ እንቅስቃሴ ማለት ምን ማለት ነው?**

ተማሪዎች ነጻ እንቅስቃሴዎች ምን ማለት እንደሆነ
ታውቃላችሁ፤ የምታውቁትን ለመምህራችሁ አስረዱ።።

## መልመጃ አንድ

1. ሁልጊዜ እነዚህን እንቅስቃሴዎች መለማመድ ያስፈልጋል፡፡

- እርምጃ፣ ሶምሶማ (ቀስ ያለ ሩጫ)፣ ዱብዱብ ማለት፣ የእጅና የእግር እንቅስቃሴ፣ ቀስ እያሉ ቁጭ ብድግ የመሳሰሉትን፡፡

## መልመጃ ሁለት

ሰውነታችሁ ትንሽ ከተሟሟቀ በኋላ ቀጣዩን እንቅስቃሴ በህብረት አድርጉ

1ኛ. ክብ ሰርታችሁ እጅ ለእጅ ተያይዛችሁ ትቆሙና መምህራችሁ ምልክት ሲሰጣችሁ እግራችሁን ክፍት ዝርግት እያረጋችሁ አንድ ወደ ግራ አንድ ወደ ቀኝ፣ አንድ ወደ ግራ አንድ ወደ ቀኝ እያላችሁ ተንቀሳቀሱ፣ ይህንን እንቅስቃሴ ደጋግማችሁ ስሩ



2ኛ. በቆማችሁበት ቦታ ላይ ከሆናችሁ በኋላ በቀኝ ወይም በግራ እግራችሁ ጀምራችሁ ሁለት እርምጃ ወደፊት፣ ሁለት እርምጃ ወደኋላ እያላችሁ ደጋግመችሁ ተንቀሳቀሱ

3ኛ. ወደፊትም ወደኋላም ሳትሄዱ ባላችሁበት በቀኝ እግራችሁ ጀምራችሁ ዱብ ዱብ ዱብ ዱብ እያላችሁ ቆም እንደገና ዱብ ዱብ ዱብ ዱብ እያላችሁ ቆም

አንድ ሁለት ሶስት አራት ዝም

አንድ ሁለት ሶስት አራት ዝም

## መልመጃ ሶስት

የምታውቁትን የውዝዋዜ አይነት አሳዩ

## መልመጃ አራት

የሚከተሉትን የሙከራ ልምምዶች እናድርግ

- ያለምንም ሙዚቃ መወዛወዝ
- በጭብጨባ ብቻ መወዛወዝ
- እየዘፈኑ መወዛወዝ

## 1.3 ቀላል የትወና ጨዋታዎች

### ከዚህ ንዑስ ምዕራፍ የሚጠበቅ የመማር ውጤት

- የተለያዩ የጨዋታ አይነቶችን ታውቃላችሁ
- የራሳችሁንም ጨዋታ ለመፍጠር መንገድ ተገኛላችሁ
- የዕርስ በርስ ግንኙነታችሁ ይዳብራል
- የትወናን ባህሪ በመጠኑ ትረዳላችሁ

### ተውኔት ማለት ምን ማለት ነው?

ተውኔት ማለት መድረክ ላይ ወይም ቴሌቪዥን ውስጥ የሚታይ መዝናኛ ነው፡፡ ተውኔት ማለት እያዝናና፣ የሚያስተምር የጥበብ ስራ ነው፡፡

መድረክ ላይ ሆነው ወይም በቴሌቪዥን ውስጥ የሚያዝናኑ ሰዎች ደግሞ ተዋናይ ይባላሉ፡፡

### መልመጃዎች

❖ ከዚህ ቀጥሎ ያሉትን የትወና ጨዋታዎች በቡድን እና በተናጠል እየሆናችሁ ተጫወቷቸው

### መልመጃ 1፣ የማስመሰል ጨዋታዎች

- የቤት እንስሳትን፣ የዱር አውሬዎችን ድምጽ ማስመሰል
- መኪና መንዳት
- ምግብ መመገብ
- ዉሃ መጠጣት
- እንደወፍ መብረር
- ደስታን፣ሃዘንን፣ ኩረፊያን ማሳየት
- ልብስ መልበስና ማውለቀ
- ገላን መታጠብ
- ፈረስ መጋለብ
- ጥርስን መቦረሽ
- እቃ መሸከምና ማውረድ

### መልመጃ 2 የምን አየህ ጨዋታ

- አንድ ሰው ክፍል ውስጥ ያሉ ተማሪዎች ማየት

በሚችሉበት ሁኔታ ፊት ለፊት ይቆምና በሰውነቱ እየተጠቀመ አንድ ነገር ይሰራል፣ ተማሪዎችንም ምን እያደረገ እንደሆን ይጠይቃቸዋል፡፡‹‹ ትክክለኛውን መልስ የሰጠ ተማሪ አሸናፊ ወይም ጎበዝ ተብሎ ይጨበጨብለታል፡፡

### መልመጃ 3 ጭራ መቀጠል

- በጥቁር ወይም በነጭ ሰሌዳ ላይ የእንስሳ ስዕል ስሎ ጭራውን መተው፣ ከዚያም ተማሪዎቹ ስዕሉን በደንብ አድርገው ካዩት በኋላ ጠመኔ ወይም ማረከር በመያዝ አይናቸውን በመሃረብ አስረው የቀረውን ጭራ እንዲስሉ ማድረግ። በትክክል ጭራውን የሳለ ተማሪ አሸናፊ ወይም ጎበዝ ተብሎ ይጨበጨብለታል፡

### መልመጃ 4 ጆሮና አፍንጫን መያዝ

- ምልክት ሲሰጣቸው ሁሉም ተማሪዎች ሆዳቸውን ወይም ጭናቸውን አንዴ መታ በማድረግ ወዲያው በቀኝ እጃቸው ጆሮአቸውን እና በግራ እጃቸው አፍንጫቸውን መያዝ ነው። በድጋሚ ምልክት ሲሰጣቸው ሁሉም ተማሪዎች ሆዳቸውን ወይም ጭናቸውን አንዴ መታ በማድረግ ወዲያው በተቃራኒ ሁኔታ በቀኝ እጃቸው አፍንጫቸውንና በግራ እጃቸው ጆሮአቸውን መያዝ ነው። ይህንን ጨዋታ ሲደጋግሙት ከፍተኛ ሳቅ ይፈጥርላቸዋል።

### መልመጃ 5 አረንጓዴ ቢጫ ቀይ

አንድ ሰው ሶስቱን ቀለሞች እንደፈለገው እየጠራ እሱ ራሱ ግን የፈለገውን አይነት እንቅስቃሴ እያደረገ ልጆቹን በቀለማቱ

ትርጉም መነሻነት ትዕዛዙን እንዲፈጽሙ ማድረግ ነው፡፡ ከትዕዘዙ ዉጪ የሰራ ተማሪ ማለትም ቀይ ቀለም ሲጠራ የተቀመጠ ወይም አረንጓዴ ቀለም ሲጠራ የቆመ ከሆን ከጨዋታ ዉጪ ይሆናል ማለት ነው፡፡ እስከ መጨረሻው ድረስ ሳይሳሳት ትዕዛዛቱን የጠበቀ ተማሪ አሸናፊ ወይም ጎበዝ ተብሎ ይጨበጨብለታል፡፡

## 1 4 ፎቶዎችን ማጤን

### መግቢያ

ፎቶግራፍ በባለ ሁለት ቀለም ወይም ጥቁርና ነጭ እና በባለ ሙሉ ቀለም ወይም በከለር ይታተማል፡፡ በአብዛኛው መጠናቸው ጉርድ ፎቶግራፍ ወይም ሙሉ ፎቶግራፍ ተብለው ይለያሉ፡፡ በፎቶግራፍ የሠዎችን ምስል፣ የመልክዓምድርን አቀማመጥ፣ ታሪካዊ ቦታዎችን ፣ እንስሳቶችን፣ እና ሌሎችንም እንመለከታለን፡፡

## ዝርዝር አላማ

| የሚጠበቁ ዝርዝር የመማር ውጤቶች |
| --- |
| • የተመለከታችሁትን ያስተዋላችሁትን ቀላል ሥዕሎችና ፎቶግራፎችን ታስረዳላችሁ፣<br>• በአካባቢያችሁ የሚገኙትን ቀለማት ትለያላችሁ።<br>• የተሻለ ትኩረት ሰጥቶ የመመልከት ወይም የማስተዋል አቅምን ታዳብራላችሁ<br>• በተወሰነ መልኩ የመልክዓ ምድርን፣ የታሪካዊ ቦታዎችን ትለያላችሁ።<br>• ነገስታትን፣ የተለያዩ ብሔረሰቦችን፣ የተለያዩ የብሔረሰቦች አልባሳትን፣ ቅርሶችን፣ ታዋቂ ሰዎች፣ ቅርሶችን እና ሌሎችንም ታውቃላችሁ።<br>• ፎቶዎቹ ላይ በዋናነት የተነሳውን ምስል፣ ከኋላ የሚታያቸውን እያንዳንዱ ነገር ትዘረዝራላችሁ (ታጤናላችሁ)። |

## 1 የመልክዓ ምድር ፎቶ

በዚህ የፎቶግራፍ አይነት የመልከዓ ምድርን አቀማመጥ፣ ተፈጠሮን፣ እንመለከታለን።


ሥዕል.1 መልክዓ ምድር


ሥዕል.2 መልክዓ ምድር

## 2 የታሪካዊ ቦታዎች ፎቶግራፍ

በሀገራችንየተለያዩ ታሪካዊ ቦታዎች ይገኛሉ፡፡ ከዚህም በጥቂቱ የሶፍ ዑመር ዋሻ፣ የጢያ ትክል ድንጋዮች፣ የአፄ ፋሲል ግንብ፣ የአድዋ ተራሮች፣ የአባይ ወንዝ፣ ጣና ሐይቅ ወዘተ...ይገኙበታል፡፡


ሥዕል.3 የአባይ ወንዝ


ሥዕል.4 ላሊበላ


ሥዕል.5 አልነጃሺ መስጅድ


ሥዕል.6 አክሱም ሀውልት

## መልመጃ አንድ

1. መምህራችሁ የሚያሳዩአችሁን የመልክዓ ምድር ፎቶግራፍ በማጤን በምስሉ ላይ ያስተዋላችሁትን ፃፉ፡፡

2. በፎቶግራፉ ላይ የሚታያችሁን ቢያንስ ሶስት ቀለማት ግለጹ፡፡

## 3 ነገሥታት

እነዚህ ከታች የምትመለከቷቸው የሀገራችን ኢትዮጵያ ነገስታቶች ከነበሩ መሀከል የጥቂቶቹ ምስል ነው፡፡



ሥዕል.7 አጼቴዎድሮስ



ሥዕል.8 አጼሚኒሊክ



ሥዕል.9 ግርማዊ ቀዳማዊ ዓፄ ኃ/ሥላሴ

## መልመጃ ሁለት

የነገስታቶቹን ፎቶግራፍ በመመልከት የተነሳበትን ቀለም በባለ ጥቁርና ነጭ ወይም በባለቀለም መሆኑን ግለጹ፡፡

1. ስዕል.7 የተነሳበትን (የታተመበት ቀለም) በባለ

   ____________________________ቀለም ነው፡፡

2. ስዕል.8 የተነሳበትን (የታተመበት ቀለም) በባለ

   ____________________________ ቀለም ነው፡፡

3. ስዕል.9 የተነሳበትን (የታተመበት ቀለም) በባለ

   ____________________________ ቀለም ነው፡፡

## 4 የታዋቂ ሠዎች ፎቶግራፍ

### 1. አትሌቶች

ሀገራችን ታዋቂና ብርቅዬ አትሌቶች ሲሆኑ በተለያዩ ጊዜያት በሩጫው (አትሌቲክስ) ላይ በመወዳደር በማሸነፍ የራሳቸውንና የሀገራቸውን ስም ለዓለም ከፍ አድርገው ያስጠሩ አትሌቶች ናቸው፡፡ ከነዚህ በተጨማሪ ሀገራቸውን በአትሌቲክስ ያስጠሩ በርካታ አትሌቶች ይገኛሉ፡፡



ሥዕል.10 አትሌት ኮማነደር ደራርቱ ቱሉ




ሥዕል.11 ክቡር ዶ/ር አትሌት

ሻለቃ ሀይሌ ገ/ሥላሴ

## 2 ሙዚቀኞች



ሥዕል.12 የሙዚቃ አቀናባሪ

ክቡር ዶ/ር ሙላቱ አስታጥቄ



ሥዕል.13 የሙዚቃ አቀናባሪ

ኤልያስ መልካ

## 3 የቴአትር ባለሞያዎች




ሥዕል.14 ባለቅኔና ፀሐፊ ተውኔት ሎሬት ፀጋዬ ገ/መድህን



*ሥዕል.15 ክቡር ዶ/ር ተስፋዬ ገሰሰ*

## መልመጃ ሶስት

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች ፎቶዎቹን በማጤን እውነት ወይም ሐሰት በማለት መልሱ።**

1.  *የአትሌት ኮማንደር ደራርቱ ቱሉ* ፎቶግራፍ ስዕል እየሳለች ያሳየናል።

2.  በፎቶው ላይ የሚታየው የሙዚቃ መሳሪያ ከበሮ ነው።

3. 

በዚህ ፎቶ ላይ የሎሬቱ እጅ በልብሱ ተደብቋል።

4.  በዚህ ፎቶግራፍ ላይ ሁለት ባንዲራዎች ይታያሉ፡፡

## ሠዓሊያን እና ቀራጺያን

በሀገራችን የሚገኙ ጥቂት የማይባሉ ባለሙያዎች ይገኛሉ፡፡ ሥነ-ጥበብ በውስጡ የተለያዩ ክፍሎችን ይዟል ከነዚህም ጥቂቶቹ ቀለምቅብ፣ ቅርፃቅርፅ ፣ የህትመት ጥበብ፣ ዲዛይን በመባል ይለያሉ፡፡ እነዚህን የጥበብ ስራዎች የሚሠሩ ባለሙያዎች ሠአሊ፣ቀራፂ፣ የህትመት ጥበብ ባለሙያ በመባል ይጠራሉ፡፡

**1.የቀለም ቅብ ባለሙያው** - ሠዓሊ በመባል ይጠራል፡፡





*ሥዕል.16 እጅግ የተከበሩ የአለም ሎሬት ሜትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ ፎቶግራፍና የሠዐሊው የቀለም ቅብ ስራ፡፡*

## 2. የቅርፃ-ቅርፅ ባለሙያው - ቀራፂ በመባል ይጠራል፡፡





*ሥዕል.17 ረዳት ፕሮፌሰር በቀለ መኮንን (ቀራፂ) ፎቶግራፍና የቀራፂው የቅርፃ-ቅርፅ ስራ*

## 3. የህትመት ጥበብ ባለሙያው- የህትመት ጥበብ ባለሙያ በመባል ይጠራል፡፡





*ሥዕል.18 ሠዓሊ ዘሪሁን የትምጌታ ፎቶግራፍና የሰዓሊው የስእል ስራ*

### መልመጃ አራት

መምህራችሁ የሚያሳዩአችሁን የተለያዩ ታዋቂ የስነ-ጥበብ ባለሙያዎች የሠሯቸውን ስራዎች ፎቶግራፍ በመመልከት በምስሎቹ ላይ የሚታያችሁን ዘርዝራችሁ ግለጹ፡፡


ሥዕል.19 በሰዓሊ ብስራት ሽባባው የተሳለ


ሥዕል.20 በሰዓሊ መዝገቡ ተሰማ የተሳለ


ሥዕል.21 በሠዓሊ ታደሰ መስፍን የተሳለ


ሥዕል.22 በሠዓሊ ደስታ ሀጎስ የተሳለ

## መልመጃ አምስት

መምህራችሁ የሚያዘጋጁላችሁን ፎቶዎች በመመልከት በቡድን የምትመለከቱትን አስረዱ።

## መልመጃ ስድስት

የሚከተሉትን ፎቶግራፎች በማየት አዛመዱ

<u>ሀ</u> <u>ለ</u>

1 የላሊበላ ፍልፍል አቢያተ ክርስቲያን



ሀ.

2 አል-ነጃሺ መስጅድ



ለ.

3 የአጼ ፋሲል ግንብ



ሐ.



4 የአክሱም ሀውልት መ .



5 የጢያ ትክል ድንጋይ ሠ.



6 የሀረር በር ረ.

## 1.5 በየእለቱ የሚለማመዷቸው ምስሎች

በዚህ ክፍለ ትምህርት ተማሪዎች ምስሎችን ከመለማመዳችሁ ባሻገር በመጀመሪያ ምስሉን በሚገባ ማየትና ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ ይህን ማድረግ ደግሞ የምስሉን ምንነት ለመረዳትና ለመለየት ይረዳል፡፡ ይህም ከመለማመዳችን ባሻገር በቅርብ ያሉትን ነገሮች አያይዘን እንድናስተውልና ያላቸውን አንድነትና ልዩነት እንድንገነዘብ ጭምር ያግዛል፡፡

**የሚጠበቁ ዝርዝር የመማር ውጤቶች**

- የመኖሪያ አካባቢያችሁን በማጤን በአካባቢያችሁ ብቻ የሚገኙ የተለዩ ነገሮችን ትለያላችሁ፤
- በአጠቃላይ ጥንቃቄ ማድረግ የሚገባችሁ ነገሮችን ለይታችሁ በማወቅ ጥንቃቄ ታደርጋላችሁ፤
- በየእለቱ የምትመለከቷቸውን ምስሎች ትስላላችሁ

## 1.5.1 ተክሎች

የተስተካከለ (መልካም) የአየር ንብረት እንዲኖረን የሚያደርጉ ተፈጥሮአዊ ሃብቶቻችን መሆናቸው ይታወቃል፡፡(ስለዚህ በአካባቢያችን የሚገኙ የተለያዩ የተክል አይነቶችን አስተውለን ልንመለከታቸው እና ልንንከባከባቸው እንዲሁም በአቅራቢያችን ከሚገኙ ጉዳት የሚያስከትሉ የተክል አይነቶችን ለይቶ ማወቅ ጭምር ይገባል፡፡)

**የሚጠበቁ ዝርዝር የመማር ውጤቶች**

- በአካባቢያችሁ የሚገኙ የተክሎች ወይም የእፅዋት አይነቶችን፣ ጠቀሜታቸውንና መደረግ ያለበትን እንክብካቤ ትረዳላችሁ፤
- የተለያዩ ተክሎችን መሳል ትለማመዳላችሁ



ሥዕል.1 አበባ



ሥዕል.2 የዛፍ

## መልመጃ 1

1. የምትፈልጉትን የዛፍ እና (የአበባ) አይነቶች ሳሉ፡፡

## 1.5.2 ቁሳቁሶች

ለተለያዩ ግልጋሎት የምንጠቀምባቸው ቁሳቁሶችን በቤታችንና በአካባቢያችን ይገኛሉ፡፡

### ዝርዝር ዓላማ

**የሚጠበቁ ዝርዝር የመማር ውጤቶች**

- በአካባቢያችሁና በቤታችሁ የሚገኙ ቁሳቁሶችን አገልግሎታቸውን ትረዳላችሁ፤
- ተሰብሪ የሆኑ ቁሳቁሶች ትለያላችሁ ትስላላችሁ፤
- በየእለቱ የምትመለከቷቸውን ምስሎች ትስላላችሁ



ሥዕል. 3 ቁሳቁሶች

### መልመጃ 2

በቤታችሁ ወይም በአካባቢያችሁ የሚገኙ የምትጠቀሙባቸውን የተለያዩ ቁሳቁሶችን መርጣችሁ ሳሉና አገልግሎታቸውንም ፃፉ፡ ፡ ምሳሌ፡- ማንኪያ፣ሹካ፣ወንበር ፡ጠረጴዛ

## 1.5.3. ተሽከርካሪ

የተለያዩ የተሽከርካሪ አይነቶችን መለየት

### ዝርዝር ዓላማ

| የሚጠበቁ ዝርዝር የመማር ውጤቶች |
| --- |
| • የተለያዩ የተሽከርካሪ አይነቶችን ልዩነታቸውን ትረዳላችሁ፤<br>• ልዩ ልዩ ተሽከርካሪዎችን መሳል ትለማመዳላችሁ |




*ሥዕል.4 አውቶብስ*




*ሥዕል.5 አነስተኛ መኪና*



*ሥዕል.6 የጭነት መኪና*



*ሥዕል.7 ባጃጅ*



*ሥዕል.8 ሞተር ብስክሌት*



*ሥዕል.9 ብስክሌት*

## መልመጃ 3

የተሽከርካሪ አይነቶችን መሳል ተለማመዱ።

- አነስተኛ መኪና፣ ሞተር ብስክሌት፣ የጭነት መኪና፣ ባጃጅ፣ ብስክሌት

## 1.5.4 ቤት

ቤት ለሰዎች መኖሪያነት መጠለያነት እንገለገልበታለን።

## ዝርዝር ዓላማ

**የሚጠበቁ ዝርዝር የመማር ውጤቶች**

- በምስልና በአካባቢያችሁ የተመለከታችሁትን የቤት አይነቶችና ልዩነታቸውን እንዲሁም የሚሠሩበትን የቁስ አይነቶች ትገነዘባላችሁ፤
- የተለያዩ የቤት አይነቶችን መሳል ትለማመዳላችሁ



ሥዕል.10 የጐጆ ቤት



ሥዕል.11 የቤት



ሥዕል.12 ህንፃ

## መልመጃ 4

በአቅራቢያችሁ ያለ የቤት አይነቶችን መሳል እና የሳላችሁትን የቤቶች አይነት ጐጆ ቤት፣ ቤት፣ ህንፃ በማለት ግለፁ።

## 1.5.5 ሰው

ሰው ህይወት ያለው የሚንቀሳቀስ፣ ማሠብ የሚችል፣ ማዳመጥ፣ መናገር የሚችል ፍጥረት ነው።

### ዝርዝር ዓላማ

| የሚጠበቁ ዝርዝር የመማር ውጤቶች |
| --- |
| • የተለያዩ ሰዎችን የሴት፣ የወንድ፣ የህፃናት፣ የአዛውንት ስዕል መሳል ትለማመዳላችሁ |

ሴት፡- ከትከሻዋ ጠበብ ብላ ከዳሌዋ ሰፋ ትላለች።

ወንድ፡- ከትከሻው ሰፋ ያለ ከዳሌው ጠበብ ይላል።



ሥዕል.13 ሴት



ሥዕል.14 ወንድ



ሥዕል.15 ህፃናት

ህፃናት፡- በመጠኑ አነስተኛ የሆነ/የሆነች

እነዚህ በአንድ ላይ ሲቀናጁ ቤተሠብ ይሆናሉ፡፡

**መልመጃ 5**

የራሳችሁን ቤተሠብ እናት፣ አባት፣ እህት፣ ወንድም፣ ሳሉ፡፡

## 1.5.6 እንስሳት

ህይወት ያላቸው እና መናገር የማይችሉ ሲሆኑ የቤት እና የዱር በመባል ይታወቃሉ ወይም ይለያሉ፡፡

**ዝርዝር ዓላማ**

**የሚጠበቁ ዝርዝር የመማር ውጤቶች**

- በዱር እና የቤት እንስሳትን ልዩነት ትረዳላችሁ፣ መሳል ትለማመዳላችሁ

ምሳሌ፡- 1) የቤት እንስሳት፡- ውሻ፣ ድመት፣ ፍየል፣ በግ፣ላም፣ በሬ ወዘተ...... ናቸው፡



ሥዕል16. ውሻ



ሥዕል.17 ድመት

2) **የዱር እንስሳት፡-** አንበሳ፣ ነብር፣ ጅብ፣ ዋሊያ፣ ቀይቀበሮ ወዘተ…… ናቸው፡፡



ሥዕል.18 አንበሳ



ሥዕል.19 ቀይ ቀበሮ

## 1.5.7 አእዋፍት



ሥዕል.20 ወፍ



ሥዕል.21 እርግብ

### መልመጃ ስድስት

የምታውቋቸውን የቤትና የዱር እንስሳት፣ አእዋፍ ሳሉ፡፡

### የማጠቃለያ መልመጃ

ከዚህ ቀደም በተማርናቸው መሠረት የተክሎች፣ የቁሳቁስ፣ የተሽከርካሪ ፣የሰው የእንስሳት ቤት እንዲሁም የአእዋፍት ምስሎች በመምረጥና በማቀናጀት የፈለጋችሁትን ስዕል ሳሉ፡፡

ምሳሌ፡- 1) ቤት፣ሠው፣ተክል

2) ዛፍ፣ እንስሳት፣ ሰው

3) አእዋፍት፣ ዛፍ፣እንስሳት

## ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ላይ ገፅ በገፅ መምህራችሁን ከተከታተላችሁ ኖታዎችን ትለያላችሁ። የኖታ አቆጣጠር ዘዴዎችን አይታችኋል ነጻ እንቅስቃሴ/ ውዝዋዜ ማለት ምን እንደሆን እና እንዴት በቀላሉ እንደሚከወን በተግባር አይታችኋል፡፡ ስለሆንም በዚህ ክፍለ ጊዜ ብቻ ሳይሆን በማንኛውም የዘውትር እንቅስቃሴአችን ውስጥ ውዝዋዜን መለማመድ አስፈላጊ መሆኑን ተገንዝበን ያለማንም ተነሳሽነት በራሳችን ፍላጎት ብንተገብረው ከዚህ የተሸለ ብቃት ይኖረናል፡፡ በየእለቱ በምስልም ሆነ በአካል የሚመለከቷቸውን ከመለማመድ ባለፈ ማስተዋል እና መለየት እንደሚኖርባችሁ ተገንዝባችኋል፡፡

በሀገራችሁ ያሉትን ነገሮች ለማወቅ፣ አካባቢያችሁን ማጤን፣ ቀለምን፣ ባህልን፣ ቅርሶችን፣ ክብረ-በዓላትን የተለያዩትን፣ ሙያተኞችን የባህል አልባሳትን መለየት አለባችሁ።

# ምዕራፍ 2

## ፈጠራን መግለፅ

### መግቢያ

ልጆች ከቤተሰቦቻቸውም ይሁን ከ አካባቢያቸው ያዩትን ማንኛውንም ነገር መልሰው መተግበር እንደሚወዱ ይታወቃል፡ አልፎ አልፎ አላስፈላጊ እና ከልጆች ስነ ልቦና ጋር አብሮ መራመድ የማይችሉ ጉዳዮችንም ከታላላቆቻቸው ወርሰው ተግባራዊ የሚያደርጉ ልጆችንም ማየት የተለመደ ነው፡፡ ስለሆነም ልጆች መቅዳት ያለባቸውን ድርጊት እየለዩ እና መልካም የሆነውን እንዲያጎለብቱ ማድረግ የሁሉም ህብረተሰብ ሀላፊነት ነው፡፡

በተለይ በ ክወናና የዕይታ ጥበባት ዘርፍ ልጆች ያላቸውን ተሰጥኦ እና ፍላጎት በደንብ አጢኖ እንዲያዳብሩት ከማድረግም በላይ የራሳቸውንም የመፍጠር ብቃት እየመረመሩ በትምህርት እንዲታገዙ ማድረግ የተተኪ ተውልድን የወደፊት ጠንካራ ህልውና ከወዲሁ ማሳደግ ጥያቄ የሌለው ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡

## ከዚህ ምዕራፍ የሚጠበቅ የመማር ውጤት

- የሙዚቃ ኖታዎችን እየቆጠራችሁ ትለማመዳላችሁ
- የቀላል መዝሙሮችን ሃሳብ ወይም መልክት ትረዳላችሁ
- በራሳችሁ ፍላጎት የትወና ጨዋታዎችን ትጫወታላችሁ
- በፈለጋችሁት ሙዚቃዎች ውዝዋዜን ትለምዳላችሁ
- መስመሮችን መሞነጫጨር እና ስእሎችን መቀባት ትችላላችሁ

## 2.1 የሙዚቃ ኖታዎች

### ከዚህ ርእስ በኋላ የሚጠበቅ የመማር ውጤት

- የሙዚቃ ኖታዎች ማንበብ ትለማመዳላችሁ።
- አራቱንም የሙዚቃ ኖታዎች ለየብቻ ታነባላችሁ።
- አራቱን ኖታዎችን ተቀላቅለው ማንበብ ትችላላችሁ።
- ኖታዎችን በደብተራችሁ ላይ መፃፍ ትለምዳላችሁ።

### መዝሙር አንድ 1

መማር መማር ዛሬም መማር

መማር መማር ነገም መማር

ጥበብ ነውና ለሀገር ክበር

ፍቅር ነውና የሀገር ሚሰጥር

ተምሬ ተመራምሬ

እሰራለሁ ለናት ሀገሬ

ተማሪው ተመራማሪው

ሳይሳን ጥበብ አክባሪው

አስተማሪው ተማሪው

አርሶ አደሩ ምሁሩ

ሊሰራ ዛሬም ለክብሩ ቆርጦ ተነስቷል ለእናት ሀገሩ

❖ የዚህ መዝሙር መልእክት ሁሉም ተማሪ ለአገሩም ለራሱም ፍሬያማ ለመሆን ጠንክሮ መማር እዳለበት ያስረዳል። በተለያየ ዘርፍ ስራም ላይ ያሉ ሰዎችም ለአገራቸው ጠንክረው እዲሰሩ መልክት ያስተላልፋል።

❖ የመዝሙሩን ዜማ ከመምህራችሁ ታገኛላችሁ

## መልመጃ አንድ

ሙሉ የድምፅ ኖታን እና ሙሉ የእረፍት ኖታን በምዕራፍ አንድ ላይ በተለማመድናቸው የኖታ አነባበብ መሰረት መምህራችን እነዚህን ኖታዎች በምሳሌ ቀጣጥለው ሲያነቡ ማዳመጥ።በተረዳችሁት ምሳሌ መሰረት ኖታዎቹን ማንበብ



ታ ____ ታ ____ ታ ____ ታ ____ ታ ____



1 2 3 4 1 2 3 4 1 2 3 4 1 2 3 4 1 2 3 4

## መልመጃ ሁለት

ሙሉ የድምፅ ኖታን እና ሙሉ የእረፍት ኖታን ተቀላቅለው መምህራችሁ ካስረዱ በኋላ መልሳችሁ ታነባላችሁ።



ታ ____ 1 2 3 4 ታ ____ 1 2 3 4 ታ ____

1 ሙሉ የድምፅ ኖታን እና ሙሉ የእረፍት ኖታን ፃፉ።

## መልመጃ ሶስት

ግማሽ የድምፅ ኖታን እና ግማሽ የእረፍት ኖታን በምዕራፍ አንድ ላይ በተለማመድናቸው የኖታ አነባበብ ዘዴ መሰረት መምህራችሁ እነዚህን ኖታዎች በምሳሌ ቀጣጥለው ሲያነቡ ማዳመጥ። በተረዳቹት ምሳሌ መሰረት ኖታዎቹን ማንበብ።



ታ___ ታ___ ታ ___ ታ ___ ታ ___



1 2 1 2 1 2 1 2

**መልመጃ አራት**

ግማሽ የድምፅ ኖታ እና ግማሽ የእረፍት ኖታን

ተቀላቅሎ መምህራችን በምሳሌ ካሰረዱ በኋላ

መልሳችሁ

ኖታዎቹን ታነባላችሁ::



1 2 ታ___ 1 2 ታ___ 1 2

**መልመጃ አምስት**

ግማሽ የድምፅ ኖታን እና ግማሽ የእረፍት ኖታን ፃፉ::

**መልመጃ ስድስት**

መምህራችሁ የሚፅፉትን ኖታዎች በደብተራችሁ ላይ ፃፉ::

**መልመጃ ሰባት 7**

የሚከተሉትን ቃላቶች በግማሽ ኖታ የአጨዋወት ዘዴ በቡድን

እና በተናጠል ማሳየት::

𝅗𝅥 𝅗𝅥 𝅗𝅥 𝅗𝅥 𝅗𝅥 𝅗𝅥 𝅗𝅥
ሙ ዚ ቃ እ ና ጥ ና

2 𝅗𝅥 𝅗𝅥 𝅗𝅥 𝅗𝅥 𝅗𝅥 𝅗𝅥
ተ ነ ሱ ለ ስ ራ

3 𝅗𝅥 𝅗𝅥 𝅗𝅥 𝅗𝅥 𝅗𝅥 𝅗𝅥
አ ዲ ስ አ በ ባ

4 𝅗𝅥 𝅗𝅥 𝅗𝅥 𝅗𝅥 𝅗𝅥 𝅗𝅥 𝅗𝅥
ው ብ ከ ተ ማ ች ን

5 𝅗𝅥 𝅗𝅥 𝅗𝅥 𝅗𝅥
ፓ ራ ፓ ፓ

## መልመጃ ስምንት

- ሁሉንም ኖታዎች በከለር ቃላት መጥራት፡፡

𝅝 𝅗𝅥 𝅗𝅥 𝅗𝅥 𝅝

አ ረ ን ጓ ዴ

  

ቢ ጫ

  

ቀ ይ

## የመልመጃ ጥያቄዎች

ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክተኛውን መልስ ምረጡ

1 ሙሉ የድምፅ ኖታ ስንት ምት አለው

ሀ. ሶስት

ምት ለ. አራት ምት ሐ. አንድ ምትመ.

ሁለት ምት

2 ሙሉ የድምፅ ኖታ እና ግማሽ የድምፅ ኖታ በምን

ይለያያሉ፡፡

ሀ. ሁለቱም ኖታ ናቸው፡፡

ለ. ሁለቱም የቁጥር መጠናቸው የተለያየ ነው፡፡

ሐ. ሁለቱም ቅርፃቸው አንድ አይነት ነው፡፡

መ. ሀ እና ለ

3 የግማሽ እረፍት ምልክት የቱ ነው

ሀ.        ሐ. 

ለ.        መ. ሀ እና ለ

4. የግማሽ የድምፅ ኖታ እና የሙሉ እረፍት ኖታ ምልክት የቱ ነው

ሀ.        ሐ. 

ለ.        መ. ሀ እና ሐ

## 2.2 ነፃ እንቅስቃሴ ወይም ውዝዋዜዎች

### ከዚህ ንዑስ ርዕስ በኋላ የሚጠበቅ የመማር ውጤት

- ለውዝዋዜ ያለችሁ ፍቅር ያድጋል
- የውዝዋዜ ለምምድ ድፍረት ታገኛላችሁ
- ውዝዋዜዎችን በፍላጎታችሁ ትለምዳላችሁ
- የውዝዋዜ ክህሎት ታዳብራላችሁ
- እያንጎራጎራችሁ መወዛወዝ ትለምዳላችሁ
- የብሄረሰብ ውዝዋዜ ትሞክራላችሁ

ውዝዋዜ ሰውነትን የሚያፍታታ እንቅስቃሴ ከመሆንም ባለፈ ደስተኛ፣ ጠንካራ እና ጤናማ እንድንሆን ማድረግ የሚችል ጥበብ ነው፡፡ ስለዚህ እናንተም የተለያዩ ውዝዋዜዎችን ሁለጊዜ እየተለማመዳችሁ አእምሮአችሁን ማጎልበት ይኖርባቹሃል

### መልመጃ አንድ

የሰውነት ማሟሟቂያ እንቅስቃሴዎችን ደጋግማችሁ ስሩ፡፡

### መልመጃ ሁለት

ይህንን ዜማ በጋራ እያዜማችሁ መምህራችሁ በሚያሳየችሁ መንገድ በጋራ እየደጋገማችሁ ተንቀሳቀሱ፡፡

እንቀሳቀሳለሁ ወደ ግራ ወደ ግራ እንዲህ እንዲህ
እንቀሳቀሳለሁ ወደ ቀኝ ወደ ቀኝ እንዲህ እንዲህ
ደሞ ወደ ፊት አንድ ሁለት
ደሞ ወደ ኋላ አንድ ሁለት
እጆቼን ወደ ላይ ደሞ ወደፊት
ደሞም እንዳሞራ ክንፍ ክንፍ

በሃይሉ ዘለቀ 2013

### መልመጃ ሶስት

ይህንን ዜማ በጋራ እያዜማችሁ መምህራችሁ በሚያሳየችሁ መንገድ በጋራ እየደጋገማችሁ ተንቀሳቀሱ

ኢትዮጲያዊ ነኝ እኔ እኮራለሁ

ባገሬ ባህል እጨፍራለሁእደንሳለሁ እወዛወዛለሁበናት

ሀገሬ እደሰታለሁከዚህ የሚበልጥ ምን አገኛለሁ

በሃይሉ ዘለቀ 2013

## መልመጃ አራት

በቡድ በቡድን እየሆናችሁ የምታውቁትን የውዝዋዜ አይነት

በክፍላችሁ ውስጥ አሳዩ

## መልመጃ አምስት

እያንዳዳችሁ ለየብቻ ሆናችሁ የዳንስ ትርዒት ለመመህራችሁ

እና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ

## መልመጃ ስድስት

የተለያዩ የብሄር ብሄረሰብ ውዝዋዜዎችን እየተለማመዳችሁ

ለመምህራችሁ እና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አሳዩ፡፡

## 2.3 የትወና ጨዋታዎች

**ከዚህ ንዑስ ምዕራፍ የሚጠበቅ የመማር ውጤት**

- ቀላል ትወናዎችን መስራት ትችላላችሁ
- ድምጻቸውን እየቀያየሩ መተወን ትለምዳላችሁ
- ትወናን በድፍረት መከወን ትችላላችሁ

### ተውኔት

1ኛ. ተውኔት ወይም ድራማ ምን እንደሆን ለመምህራችሁ እና ለክፍለ ጓድኞቻችሁ ንገሯቸው፡፡

2ኛ. አንድ ሰው ጎበዝ ተዋናይ ለመሆን ከፈለገ ምን ማድረግ አለበት፤

የዚህን ጥያቄ መልስ ለመምህራችሁና ለክፍል ጓደኞቻችሁ ንገሯቸው



ልጆች ድራማ እየሰሩ

## የትወና ልምምድ ለተማሪዎች

1ኛ. የትወና ልምምድ ለማድረግ መጀመሪያ ፍርሃትን ማስወገድና ደፋር መሆን አለባችሁ፡፡

2ኛ. በአካባቢያቸውን የሚገኙትን ነገሮች በደንብ ማየትና ማስታወስ አለባችሁ፡፡

3ኛ. የሰዎችን አነጋገር፤ እንቅስቃሴ፤አለባበስ በሚገባ ማየት አለባችሁ፡፡

4ኛ. ፊልሞችን እና ድራማዎችን ማየትና ያያችሁትን መለማመድ አለባችሁ፡፡

5ኛ. የተለያዩ ሰዎችን እና እንስሳትን እያስመሰላችሁ መለማመድ አለባችሁ፡፡

### መልመጃ አንድ

1ኛ ቀደም ሲል የምታውቁትን ቀልዶች ለጓደኞቻችሁ እና ለመምህራችሁ ንገሯቸው

2ኛ የምታውቁትን ተረት ድምጻችሁን ከፍ አድርጋችሁ አውሩ

3ኛ ከምታውቁት ተረት ውስጥ አንዱን ገጸባህሪ ምረጡ

4ኛ የመረጣችሁትን ገጸባህሪ እያስመሰላችሁ አውሩ

5ኛ ፊልም ላይ አይታችሁ የወደዳችሁትን ገጸባህሪ ግለጹ

6ኛ የመረጣችሁትን ገጸባህሪ እያስመሰላችሁ አውሩ

## ቀጥሎ ከሚታዩት ምስሎች የተረዳችሁትን ለመምህራቹ እና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አስረዱ

1.





## መልመጃ ሁለት

1ኛ. ድምጻችሁን እየቀያየራችሁ አውሩ

ወንዶቹ እንደሴት፡- ሴቶች ደግሞ እንደወንድ

2ኛ. እንደትላልቅ ሰው እየተንቀሳቀሳችሁ አውሩ፡-

እንደ እማማ፣ እነደ አባባ፣ እንደ ጋሼ፣ እንደ እትዬ

3ኛ. እንደ እንስሳት ሆናችሁ ድምፅ አውጡ

እንደ ድመት. እንደ ውሻ፣ እንደ በግ፣ እንደ ፍየል.

እንደ ዶሮ ወዘተ

## መልመጃ ሶስት

ከዚህ ቀጥሎ የተጻፉትን ተውኔቶች ከጓደኞቻችሁ ጋር እየተለማመዳችሁ ክፍል ውስጥ ትሰራላችሁ

## ተውኔት አንድ

### እንቅልፋሙ ልጅ

**እንቅልፋሙ ልጅ፡-** እህቴ

**እህት፡-** አቤት

**እንቅልፋሙ ልጅ፡-** ቶሎ ቶሎ በይ ትምህርት ቤት እንሂድ

**እህት፡-** ሄጄ መጣሁ እኮ

**እንቅልፋሙ ልጅ፡-** ለምን መጣሽ

**እህት፡-** ትምህርት አልቆ ነዋ 11 ሰዓት ሆኗል እኮ

**እንቅልፋሙ ልጅ፡-** ለምን ብቻሽን ሄድሽ

**እህት፡-** አንተ እንቅልፍህን ለጥ ብለህ ተኝተህ ነዋ

## ተውኔት ሁለት

### ድመቷ እና ውሻው

**ውሮ፡-** አነተ ቡቺ

**ውሻው፡-** እ ምን ላርግሽ

**ውሮ፡-** ሳንባዬን ማነው የበላብኝ

**ውሻው፡-** እኔ ነኝ፤ ምን ታመጫለሽ

**ውሮ፡-** ወይኔ እ እ እ ለምን በላህብኝ

**ውሻው፡-** እራበኛ፡፡

**ውሮ፡-** ታዲያ የራስህን ምግብ አትበላም ነበር

| | |
|---|---|
| ውሻው፡- | እኔ እኮ በቀን አንዴ ብቻ ነው የምበላው አንቺ ሰዎች ምግብ ሲበሉ እግራቸው ስር ቁጭ ብለሽ ሲወረውሩልሽ እያነሳሽ እንክት ታደርጊያለሽ |
| ውሮ፡- | ቆይ እናገርብሃለው |
| ውሻው፡- | ተናገሪ አልፈራም፤ አሁንማ ጥግብ ብያለሁ |
| ውሮ፡- | እ እ እ ሳንባይን በላብኝ እ እ እ |
| ውሻው፡- | ኪ ኪ ኪ ኪ አለቀሰች ቂ ቂ ቂ ቂ |
| | ተፈጸመ በሃይሉ ዘለቀ 2013 |

**እንቅልፋሙ ልጅ፡-** ወይኔ ጉዴ፤ እስካሁን ተኝቼ ነው፡፡ እ እ

ተፈጸመ በሃይሉ ዘለቀ 2013

ከድራማው ምን ሃሳብ እንዳገኛችሁ ለመምህራችሁና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አስረዱ፡፡

## መልመጃ አራት

የሚከተሉትን ገጸባህሪያት እየተቀያየራችሁ ተለማመዷቸው፡፡

- አባትና ልጅ — ወንድምና እህት
- እናትና ልጅ — እህታማቾች
- አባትና እናት — ወንድማማቾች

## 2.4 በመስመር መሞነጫጨርና መስመር መሳል

### የሚጠበቁ ዝርዝር የመማር ውጤቶች

- የሞነጫጨሩንና በመስመር የሳሏቸውን ሥዕሎች ታሳያላችሁ::
- የመስመር አይነቶችንና ስያሜያቸውን ትለየላችሁ ትስላላችሁ::

## 2.4.1 በመስመር መሞነጫጨር

### የሚጠበቁ ዝርዝር የመማር ውጤቶች

- ነጻ ሆናችሁ እጃችሁን ታለማመዳላችሁ ወይም መስመርን ትሞነጫጭራላችሁ::
- ወጥ በሆነ መስመር መስራትን ትችላላችሁ::
- በነጻነት የሰራችሁትን መስመር ከለር ፓስትል /ጭቃ ከለር/ ክራዮን በመጠቀም ትቀባላችሁ::

መስመር መሞነጫጨር በፍጥነትና በግዴለሽነት ወይም ያለ ምንም መጨናነቅ ለመሳል ወይም ለመጻፍ እጃችንን የምናፍታታበት የመለማመጃ መንገድ ነው ::

## መልመጃ አንድ

ከታች የምትመለከቱትን የመስመር አይነት እንዴት እንደምትሰሩ ከመምህራችሁ ካያችሁ በኋላ እየደጋገማችሁ ትለማመዳላችሁ፡፡



ስዕል. 1 በመስመር መሞነጫጨር

## መልመጃ ሁለት

ከታች በምትመለከቱት ምሳሌ መሰረት የሚከተሉትን እጃችሁ ሳይነሳ መስመር ከሰራችሁ በኋላ የተለያየ ከለር መርጣችሁ ትቀባላችሁ፡፡





ስዕል. 2 በመስመር

## 2.4.2 መስመር መሳል

**የሚጠበቁ ዝርዝር የመማር ውጤቶች**

- የተለያዩ የመስመር አይነቶችን ቋሚመስመር ፣የአግድም መስመር ፣ማዕበል የመሰለ መስመር ፣ባለነጠብጣብ መስመር እና የተቆራረጠ የአግድመት መስመር ፣ዚግዛግ ፣ደመና የመሰለ መስመር ፣የተቆራረጠ ሰያፍ መስመር ፣ማዕዘን ያለው ጥምዝምዝ መስመር፣ ቀጭን መስመር ፣ ወፍራም መስመር ፣ ሰያፍ መስመር ፣ግማሽ ክብ መስመሮችን ትስላላችሁ።

መስመር በተለያየ አቅጣጫ የሚሰመር ሲሆን ይኸውም ከላይ ወደ ታች ወይም ከታች ወደ ላይ፣ ከግራ ወደ ቀኝ እንዲሁም የተለያየ አቅጣጫ በማስመር የሚገለጽ ነው።



ስዕል.3 የተለያዩ የመስመር አይነቶች

1. **ቋሚ (ቀጥታ) መስመር፡-** ያለ ምንም ማዘንበል ቀጥ ብሎ ከታች ወደ ላይ የሚሔድ የመስመር አይነት ነው። ይህም መስመር ቁመትን ያመለክታል።



*ስዕል.4 ቋሚ (ቀጥታ) መስመር*

2. **የአግዳሚ መስመር፡-** ቀጥ ብሎ ወደ ጎን ከግራ ወደ ቀኝ ወይም ከቀኝ ወደ ግራ የሚሄድ የመስመር አይነት ሲሆን ስፋትን ወይም ርቀትን እንገልጽበታለን።



*ስዕል.5 የአግድመት መስመር*

3. **ሰያፍ መስመር፡-** ቀጥ ያለ ሰያፍ በግራ ወይም በቀኝ አቅጣጫ የሚሄድ የመስመር አይነት ነው።



*ስዕል.6 ሰያፍ መስመር*

4. **ዚግዛግ መስመር፡-** በተቃራኒ አቅጣጫ ያሉ የሁለት ሰያፍ መስመሮች ጫፍ በመደጋገም ስናገጣጥም የምናገኘው የመስመር አይነት ነው ፡፡



ስዕል.7 ዚግዛግ መስመር

5. **ታጣፊ መስመር፡-** በተለያየ አቅጣጫ የሚታጠፍ የመሰመር አይነት ሲሆን ያልተረጋጋ ወይም ማዕበል የሚመስል ወይም እየተጥመለመለ የሚሄድ የመስመር አይነት ነው፡፡





ስዕል.8 ደጋን መስመር

## መልመጃ ሦስት

መምህር የመስመር አይነቶች ቋሚ መስመር፣ የአግድመት መስመር፣ማዕበል የመሰለ መስመር፣ ባለነጠብጣብ መስመር እና

የተቆራረጠ የአግድመት መስመር፣ ዚግዛግ፣ ደመና የመሰለ መስመር፣የተቆራረጠ ሰያፍ መስመር፣ማዕዘን ያለው ጥምዝምዝ መስመር፣ቀጭን መስመር፣ወፍራም መስመር፣ ሰያፍ መስመር ፣ግማሽ ክብ መስመርን ትስላላችሁ፡፡

### 2.4.3 መስመሮች ቅርፅ (ሼፕ) መስራት

**የሚጠበቁ ዝርዝር የመማር ውጤቶች**

- መስመሮችን በመገጣጠም ቅርጾችን (ሼፕ) ትስላላቹ፡፡
- መስመሮችንና ቅርጾችን በመገጣጠም ወደ ምስሎች ቀይራችሁ ትቀበላላችሁ፡፡

እነዚህና ሌሎች መስመሮችን በመገጣጠምና አቀማመጣቸውን በመቀያየር የተለያዩ ቅርጾችን (ሼፕ) ለመሳል ወይም ለመስራት ያስችሉናል፡፡

**መልመጃ አራት**

1. ከታች ያሉትን የተለያዩ የመስመር አይነቶች በመገጣጠም ከመምህራችሁ ካያችሁ በኋላ በምሳሌው መሰረት ቅርፆችን ተለማመዱ፡፡

2. የሰራችሁትን የተለያዩ የቅርፅ (ሼፕ) አይነቶች በመረጣችሁት ቀለም (ከለር) ቀቡ፡፡




*ስዕል.9 መስመሮችና ቅርፆች*




*ስዕል.10 የተለያዩ ቅርጾች (ሼፖች)*








ስዕል.11 ቅርፆችን በማገጣጠም የተሰሩ ስዕሎች

## ማጠቃለያ መልመጃ

1ኛ. ሙሉ የሙዚቃ ኖታ ምን አይነት እንደሆን ለመምህራችሁ አሳዩ

2ኛ.  ይህ ምስል የምንድን ነው

3ኛ. ግማሽ ኖታ ስንት ምት አለው

4ኛ መምህሩ በሚያሳያችሁ መሰረት ቅርፆችን በማቀናት ወደ ምስል መቀየርን እንዲሁም ቀለም መርጣችሁ መቀባትን ተለማመዱ።

### ማጠቃለያ

ተማሪዎች አሁን ባላችሁበት ደረጃ ኖታዎችን በሶስቱ መንገድ ተረድታችኋል። ለወደፊቱ በዚህ መንገድ ሌሎች ኖታዎችንም በቀላሉ ትረዳላችሁ። የመዝሙሮቹ ዝርዝር ሃሳቦችና መልእክቶችን ማወቅና መገንዘብ ትችላላችሁ። ለሀገር ፍቅርን፣ ጠንክሮ የመስራት ውጤትን ከወዲሁ ትገነዘባላችሁ።

ውዝዋዜ ጤነኛ እንድትሆኑ ያደርጋል። ውዝዋዜ ያዝናናችኋል፤ ውዝዋዜ ጎበዝ እና ቀልጣፋ እንድትሆኑ ያደርጋል።

ውዝዋዜ እና እንቅስቃሴ ባገኛችሁት አጋጣሚ ልትሞክሩት የሚገባ ነገር ነው።

ከላይ የተጠቀሱትንም ቀላል የትወና ጨዋታዎች በቡድን እና በተናጠል መለማመድ አለባችሁ፡፡ ከመሳቅ እና ከመዝናናት በላይ መቅሰም ያለባችሁን ክህሎት እንድትለዩ ይደረጋል፡፡ የተለያዩ የመስመር አይነቶችን አይታችኋል፡፡ ከዚህ በኋላ በሚኖራችሁ የእረፍት ጊዜም ቢሆን የተለያዩ የመስመር አይነቶችን እየተለማመዳችሁ ለቤተሰቦቻችሁም ለመምህራችሁም አሳዩ፡፡

# ምዕራፍ 3

## ታሪካዊ እና ባህላዊ አውዶች

### 3 ባህላዊ እይታ

#### መግቢያ

ባህል የአንድ ሀገር ሕብረተስብ የአኗኗር ዘይቤ ነው፡፡ የእድገት የስለጣኔ ደረጃ መገለጫ ነው፡፡ የሰርግ፤ የሐዘን፤ የአለባበስ፤ የአመጋገብ፤ ማሳያ ነው፡፡የሙዚቃ መሳሪያዎች ሙዚቃዎች ጭፈራዎች የባህል መገለጫ ናቸው፡፡

**ከዚህ ምዕራፍ የሚጠበቅ የመማር ውጤት**

**ከዚህ ምዕራፍ መጠናቀቅ በኋላ የሚከተሉትን ትችላላችሁ**

- በደረጃችሁ የባህልን ምንነት ትረዳላችሁ
- ባህላዊ ሙዚቃዎችን እና ውዝዋዜዎችን ለይታችሁ ታውቃላችሁ
- ተረቶችን ማውራት ትችላላችሁ
- ባህል ለ ክ.ዕ.ጥ መሰረት መሆኑን ትረዳላችሁ

### 3.1 አገራዊ ሙዚቃ

**ከዚህ ርዕስ በኍላ የሚጠበቅ የመማር ውጤት**

- ስለ ባህላዊ ሙዚቃ ትረዳላቹሁ፡፡

- የተለያዩ መዝሙሮችን ትዘምራላችሁ፡፡
- የመዝሙሩንም አላማ በክፍላችሁ ውስጥ ትወያያላችሁ፡፡

## አገራዊ ሙዚቃ እና ገፅታቸው

➢ ሀገራዊ ሙዚቃ ማለት ባህላዊ ቃርፃቸውን እና ይዘታቸውን ሳይለቁ የሚዘፈኑ ሙዚቃዎች ናቸው፡፡

➢ ሀገራዊ ሙዚቃ በኢትዮጲያ ውስጥ ብዙ ብሔር ብሔረሰቦች ያሉ በመሆናቸው ልዩ ልዩ ባህላዊ ሙዚቃዎች ከየብሔረሰቡ ይመነጫሉ፡፡

## ሽለላ እና ፉከራ

ሽለላ እና ፉከራ ታዋቂ የሆነ አገራዊ(ባህላዊ) ሙዚቃ ነው፡፡

ሽለላ እና ፉከራ በሀገራችን ኢትዮጵያ ሁሉም ክልል ውስጥ የሚገኝ ባህል ሲሆን ይህም ባህል የሚከወነው በተለያዩ ጊዜያት ነው፡፡

ሰዎችን ለማሞገስ እና የተለያዩ ጦርነቶች በሀገር ላይ ሲመጡ ጀግኖቻቸውን ለማበረታታት የሚከወን ባህላዊ ሙዚቃ ነው፡፡

ዘራፍ ተነስቶ ዘርፍ ሲነሳ
የለሊት አውሬ የቀን አንበሳ
በዛ ቁልቁለት በዛ ድፋታ
በአንድ እጁ ብረት በአንድ እጁ ቃታ

ከቃታም ቃታ ቃታ ሞልቃቂ

የኢትዮጵያ ልጅ ወንድ አበርካኪ

ኢትዮጵያ ሀገሬ አይዞሽ አይዞሽ

በአራቱም ማዕዘን አለሁልሽ

እቢጃ እቢጃ አምጡልኝ ሶላቶን

ልበለው ደረቱን አውሬው አውሬውን

ተማሪዎች ሽለላእና ፉከራ መምህራችሁ ያሳዩአችኋል ያያችሁትንም ተለማምዳችሁ ለትምህርት ቤታቹ ታቀርባላችሁ

## መዝሙር አንድ

ሆያ ሆዬ

ሆያ ሆዬ ሆ

ሆያ ሆዬ ሆ

ሆያ ሆዬ ሆ

ሆያ ሆዬ ሆ

አንዱን ስጪው ሆ

አትለውጪው ሆ

እዚያ ማዶ ሆ ጭስ ይጨሳል ሆ

አጋፊሪ ሆ ይደግሳል ሆ

ያንን ድግስ ሆ ውጬወጬ ሆ

በድንክ አልጋ ሆ ተገልብጬ ሆ

ያቺ ድንክ አልጋ ሆ አመለኛ ሆ

ያለአድ ሰው ሆ አታስተኛ ሆ

### የመዝሙር ትርጉም

- ሆያ ሆዬ ባህላዊ የልጆች ሙዚቃ ነው።

የምትጫወቱትም በባህል ቀን ነው ። ለምሳሌ የዘመን መለወጫ ላይ ዘመኑ ሊለወጥ ሲል አንድ ቀን ሲቀረው ማታላይ ወዶች ተሰብስበው ሰዎችን እያሞገሱ የሚዘምሩት(የሚጫወቱት) ነው።

## መዝሙር ሁለት፡- እንቁጣጣሽ

እንቁጣጣሽ እኳን መጣሽ

በአበቦች መሀል እንምነሽነሽ

እንቁጣጣሽ እኳን መጣሽ

በአበቦች መሀል እንምነሽነሽ

መስከረም ጠባ -አበባ

እሰይ እሰይ-አበባ

የደስታ ዘመን - አበባ

መልካም ፀደይ አበባ

እንቁጣጣሽ እኳን መጣሽ

በአበቦች መሀል እንምነሸነሸ

ኢትዮጵያ ሀገሬ -አበባ

የምመኝልሽ- አበባ

የሰላም ዘመን -አበባ

እዲሆንለሽ- አበባ

- የመዝሙሩን ዜማ ከመምህራችሁ ታገኛላችሁ፡፡

## የመዝሙሩ ማብራሪያ

ይህ የባህል ዘፈን የሚዘፈነው የባህል ቀን የዘመን መለወጫ ቀን ነው፡፡ እንቁጣጣሽ እንኳዋን መጣሽ ማለት መስከረም ሲጠባ ብቻ የሚወጣ አበባ ስላለች ነው፡፡ እንቁጣጣሽ እንኳዋን መጣሽ እየተባለ ሚዘፈ ዘፈን ነው፡፡ ስለዚህ መስከረም መግባቱን የምታስታውስ የተፈጥሮ አበባም ነች፡፡

### መዝሙር ሶስት

ቲክ ቶክ

ቲክ ቶክ ቲክ ቶክ

ቀንና ለሊቱ

ቲክ ቶክ ቲክ ቶክ

ይላል ሰአቱ

ቲክ ቶክ ቲክ ቶክ

ጊዜውን ለማወቅ

ቲክ ቶክ ቲክ ቶክ

ሰዓት ይጠቅማል

- የመዝሙሩን ዜማ ከመምህራቹቻችሁ ታገኛላችሁ።

### የመዝሙሩ ማብራሪያ

ሰአትን የሚያመለክት በሰዓት ውስጥ ያሉትን የሰአት መቁጠሪያዎች በሚያሽከረክሩበት ጊዜ የሚያሰሙት ድምፅ ቲክ ቶክ እያለ የሚሰማ ድምፅ ነው።

### መልመጃ

**ትክክል የሆነውን እውነት ስህተት የሆነው ሀሰት በማለት መልሱ**

1 . አገራዊ ሙዚቃ ማለት ከሌላ ሀገር ሙዚቃ ጋር የተቀላቀለ ማለት ነው።

2 . ሽለላ እና ፉከራ የማይታወቅ የተረሳ ባህላዊ ሙዚቃ ነው።

3 . ሆያ ሆዬ የሙዚቃ የልጃች የባህል ሙዚቃ ነው።

4 . ባህላዊ ሙዚቃ የአንድ ብሔረሰብ የባህል መገለጫ ነው።

5 . እንቁጣጣሽ እኩዎን መጣሽ የባህል መዝሙር ነው።

## ለሚከተሉት ጥያቄዎች ክፍት ቦታቸውን ሙሉ

1. የሌሊት ______ አንበሳ
2. _____አይዞሽ አይዞሽ
3. እቢጃ አምጡልኝ______

## 3.2 አገራዊ ውዝዋዜ

ባህላዊ እይታ የአንድ ሀገር ሕብረተሰብ የአኗኗር ዘይቤ የእድገት የስልጣኔ ደረጃ መገለጫ ናቸው። ውዝዋዜም የአንድ ብሔረሰብ አንዱ የባህል መገለጫ ነው።

➢ **አገራዊ ውዝዋዜ**

ከዚህ ርዕስ በኋላ የሚጠበቅ የመማር ውጤት

- ባህላዊ ውዝዋዜ ምን ማለት እደሆነ ታውቃላቹሁ።
- የተለያዩ ባህላዊ ውዝዋዜወዎችን ታውቃላቹሁ።

### አገራዊ ውዝዋዜ እና ገፅታቸው

➢ ውዝዋዜ ከስሜት የሚመነጭ የእንቅስቃሴ ጥበብ ነው።

ውዝዋዜ የአንድ ብሔረሰብ የባህል መገለጫ ነው።

### ኩናማ

ኩናማ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ በሰሜን ትግራይ ክልል ወራ ዞን ውስጥ የሚገኝ ብሔረሰብ ነው። ጭፈራቸውም

በእግራቸው መሬቱን በመምታት ነው።ምስሉ ላይ ያለውንም




ይመስላል

ምስሉ የተገኘው ጎግል ድህረ ገፅ ላይ ነው።

መልመጃ አንድ ፡- ባህላዊ ውዝዋዜ መምህራችሁ በተግባር ያሳያችኋል

ጎንደር፡-

ጎንደር በሰሜን ኢትዮጵያ የምትገኝ ሀገርስትሆን ብዙታሪክ ያላት ሀገር ናት። የጎንደር ባህል መገለጫዎች አንዱ ጭፈራዋ ነው። አንገት እና ትከሻን በማነቃነቅ የሚጨፈር ጭፈራ ነው። ምስሉ ላይ ያለውንም ይመስላል።መምህራችን ደግሞ በተግባር ያሳዩናል።



ምስሉ የተገኘው ጎግል ድህረ ገፅ ላይ ነው።

ሸጎዬ ፡- ሸጎዬ ሀረርጌ ውስጥ የሚገኝ ባህላዊ ውዝዋዜ ነው። የብሔረሰቡም የባህል መገለጫ ነው። ጭፈራውም አንገትና ትከሻን በማነቃነቅ ነው። ከታች የተቀመጠውን ምስል ይመስላል። መምህራችሁም በተግባር ያሳያችኋል።



ምስሉ የተገኘው ጎግል ድህረ ገፅ ላይ ነው፡፡

ሀመር ፡- የሀመር ጭፈራ ወንዶቹ በእግራቸው ከመሬት በመዝለል ሲሆን ሴቶች ደግሞ ተያይዘው በመዝለል እና እጃቸው ላይ ያለውን አምባር በማሽከርከር ነው፡፡

ጭፈራውም
የብሔረሰቡ የባህል መገለጫ ነው፡፡



ምስሉ የተገኘው ጎግል ድህረ ገፅ ላይ ነው፡፡

መልመጃ አንድ፡- ባህላዊ ውዝዋዜ በቪዲዮ መምህራችሁ ያሳያችኋል፡፡ ያያችሁትንም ትላማመዳላችሁ፡፡

## የመልመጃ ጥያቄዎች

### ትክክል የሆነውን እውነት ስህተት የሆነው ሀሰት በማለት መልሱ

1 ውዝዋዜ የአንድ ብሔረሰብ የባህል መገለጫ አይደለም፡፡

2 ሸጎዬ ሀረጌ ውስጥ የሚገኝ ባህላዊ ውዝዋዜ ነው።

3 ጎንደር በሰሜን ኢትዮጵያ የምትገኝ ሀገር ስትሆን ብዙ ታሪክ ያላት ሀገር ናት።

## 3.3 የድራማ ባህላዊ ገፅታ እና ታዋቂ ተረቶች

### ከዚህ ርዕስ የሚጠበቅ የመማር ውጤት

**ይህንን ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ የሚከተሉትን ነገሮች ትችላላችሁ**

- ተረቶችን ማውራት ትችላላችሁ።
- የተረቶችን መልዕክት ማወቅ ትችላላችሁ
- የተረቶችን ገፀባህሪያት መለየት ትችላላችሁ
- የድራማን ባህላዊ ገፅታ መረዳት ትችላላችሁ

### የድራማ ባህላዊ ገፅታ

ድራማ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ባለፉት ምዕራፎች አይታችኋል፡ አሁን ደግሞ ባህላዊ ገፅታውን እናያለን

**ተማሪዎች**፡- ባህል ሲባል ሰምታችሁ ታውቃላችሁ ምን ማለት እንደሆነ የምታውቁትን ለመምህራችሁ ንገሩ

- ባህል የድራማ የሙዚቃ እንዲሁም የስዕል ጥበባት መነሻ ነው።
- ባህል ለድራማ መነሻ የሚሆኑ ብዙ ክዋኔዎችን ይዟል።

• ከክዋኔዎቹ መካከል ደግሞ አንዱ ጨዋታ ነው ከጨዋታዎች

መካከል ደግሞ **ተረት ተረት** እና **እንቆቅልሽ** እናገኛለን፡፡

በዚህ ርዕስ ስር ታዋቂ ተረቶችን እና እንቆቅልሾችን እናያለን፡፡

## 1 ተረቶች

ተረት ለተማሪዎች በጣም አስፈላጊ ነገር መሆኑን ማወቅ አለባችሁ፡፡ ምክንያቱም ተረት ያዝናናል፣ያጫውታል፣ቁንጅ ቁንጅ ትምህርቶችን ይሰጣል፡፡

በተረት ውስጥ የሚገኙ ገፀባህሪያት ከልጆች ጋር ቅርበት ያላቸው ስለሆኑ ቶሎ አይረሱም፣ ልጆችም ተረቱን ሲሰሙ የትኛው ገፀባህሪ ምን እንዳደረገ እና ምን እንደተደረገበት ማስታወስ ይችላሉ

### ተረት ተረት 1

#### አለቃ ገብረሃና

ከለታት አንድ ቀን አለቃ ገብረሃና ድግስ ቤት ተጠርተው ሄዱ፣ ታዲያ የለበሱት ልብስ ቆንጆ ልብስ ስላልነበር ድግስ ቤቱ በር ላይ የቆሙት አስተባባሪዎች አላስገባ አሏቸው፡፡ አለቃ ተናደዱና ለምንድነው የማታስገቡኝ ብለው ሲጠይቁ አስተባባሪዎቹ ደግሞ የለበሱት ልብስ ለድግስ ቤቱ አይሆንም የሄንን ልብስ ለብሰው መግባት አይችሉም፣ ሌላ ለድግስ ቤቱ

የሚሆን ልብስ ለብሳችሁ ኑ አሏቸው፡፡ አለቃም እሺ ብለው እቤታቸው ሄደው ቆንጆ ልብስ ለብሰው መጡና ድግስ ቤቱ ውስጥ ገቡ፡፡

ከገቡ በኋላ ምግብ ሲቀርብላቸው ለራሳቸው መብላት ትተው ልብሳቸውን በምግቡ መለቅለቅ ጀመሩ፡፡ ሰዎቹም አዩቸውና ደነገጡ፣ እንዴ አለቃ ምን እያደረጉ ነው ብለው ሲጠይቋቸው አለቃም ለብሴን ምግብ እያበላሁት ነው አሉ፣ ሰዎቹም ግራ ገብቷቸው ልብሶትን ለምንድነው የሚያበሉት ብለው ሲጠይቋቸው አለቃ ፈገግ ብለው የተጠራው ልብሴ ስለሆነ ነዋ አሉ ይባላል፡፡

## መልመጃ አንድ

1. ይህንን ተረት ካነበባችሁ በኋላ ታሪኩን ለመምህራችሁና ለክፍል ጓደኞቻችሁ ንገሯቸው፡፡
2. ከተረቱ የተረዳችሁትን ነገር አስረዱ፡፡

## ተረት ተረት 2

### ነብር እና ድኩላ

በድሮ ጊዜ ነብር እና ድኩላ የተባሉ የዱር እንስሳት ነበሩ፡፡ እነዚህ እንስሳት ይፈራሩ ነበር በተለይ ድኩላ ነብርን ስለምትፈራው ገና ከርቀት ስታየው ድንብርብር ብላ ትሮጣለች፡፡

ታዲያ ከዕለታት አንድ ቀን ነብር ድኩላን ጠራትና ስሚ እኔና አንቺ ሁልጊዜ ለምን እንጣላለን; ወዳጅ ጓደኛ ሆነን ለምን አንኖርም ብሎ ጠየቃት፤ ድኩላም እንቢ ካለችው እንደሚቦጫጭቃት ስለምታውቅ እየፈራች እሺ አለችው፡፡ ከዚያም በወዳጅነት አብረው ለመኖር በመሃላ ተስማሙና መኖር ጀመሩ፡፡ ድኩላም ነብር በጣም የወደዳት መሰላትና ደስተኛ ስለሆነች በጣም ቆንጅዬ ሆነች፡፡ከድሮ አሁን አማረባት፡፡ በዚህ ጊዜ ነብር ቆንጆ መሆኗን አይቶ ለመብላት ጎመጀ፡፡

ታዲያ አንድ ቀን ጠራትና ስሚ ድኩላ አላት አቤት ጌታዬ አለችው፡፡ ነብሩም መሃላ ያፈረሰ ምን ይሆናል ብሎ ጠየቃት. ድኩላም እየፈራች አረ ምንም አይሆንም እርግማኑ በልጅ ልጁ ይደርሳል እንጂ ብላ መለሰችለት፡፡

ነብርም ጥርሱን አግጥጦ እንግዲያውስ አሁን እበላሽና እርግማኑ በልጅ ልጄ ይድረስ አላትና ዘልሎ ቁጭ አለባት፤ ድኩላም ለማምለጥ ስትታገል ቀንዷ ነብሩን ሆዱን ወጋውና አንጀቱ ተዘረገፈ፤ ነብሩም ሊሞት ሲል አንቺ ውሸታም እርግማኑ ለልጅ ልጅ ነው የሚደርሰው አላልሽም ነበር ብሎ ሲጠይቃት ድኩላዋም ምናልባት አባትህ መሃላ አፍርሶ ይሆናላ አለችው ይባላል፡፡

### መልመጃ ሁለት

1. ይህንን ተረት ካነበባችሁ በኋላ ታሪኩን ለመምህራችሁና ለክፍል ጓደኞቻችሁ ንገሯቸው።
2. ከተረቱ የተረዳችሁትን ነገር አስረዱ።
3. ይህንን ተረት በድራማ መልክ ለመስራት ሞከሩ።

## 2 እንቆቅልሾች

ተማሪዎች እንቆቅልሽ ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ

መልሱን ለመምህራችሁ እና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አስረዱ

### መልመጃ አንድ

ቀደም ሲል የምታውቋቸውን እንቆቅልሾች ጠይቁ ታዲያ

እንቆቅልሽ ስትጠያየቁ በዚህ መልኩ ነው።

ጠያቂ እንቆቅልህ ወይም ለሴት ከሆነ እንቆቅልሽ ይላል

መላሹ ምን አውቅልህ ወይም ምን አውቅልሽ ይላል

ከዚያም ጥያቄውን ያቀርባል መላሹ መልሱን ይሰጣል።

### መልመጃ ሁለት

ከዚህ ቀጥሎ ያሉትን የእንቆቅልሽ ጥያቄዎች ለመመለስ ሞክሩ

እንቆቅልህ/ እንቆቅልሽ፦

1. ያባቴ ጎረምሳ ግድግዳ የሚበሳ

2. ጠዋት በአራት እግሩ፣ቀን በሁለት እግሩ ማታ በሶስት እግሩ የሚራመድ ምንድን ነው
3. አንዴ ከወጡበት ተመልሰው የማይገቡበት
4. ከእናቷ ሆድ ወጥታ እናቷን የምትመታ
5. ሲሄድ ውሎ ሲሄድ ቢያድር የማይደክመው
6. መሶብ የምትመስል መሶብን የማታክል

## 3.4 የቀለም ባህላዊ ገፅታ

### ቀለም

በዚህ ክፍለ ትምህርት ተማሪዎች ቀለም በኢትዮጵያ ያለውን ባህላዊ ገጽታ፣ ኢትዮጵያዊያን ቀለምን እንዴት እና መቼ መጠቀም እንደጀመሩ፣ ለምን አገልግሎት እንደሚጠቀሙበትና ቀለሞች ከምን ከምን እንደሚያዘጋጁ ግንዛቤ የሚወስዱበት ትምህርት ነው፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎች የሀገራቸውን ሰንደቅ አላማ ጠንቅቀው መለየት እንዲችሉ ይጠበቃል፡፡

### 1. ዝርዝር አላማ

| የሚጠበቁ ዝርዝር የመማር ውጤቶች |
|---|
| • የቤተሰቦቻችሁንና የጓድኞቻችሁን የልብስ ቀለማትን ትለያላችሁ<br>• የሀገራችሁን ሰንደቅ አላማ ቀለም ትለያላችሁ |

## 3.4.1 የቀለም ጅማሬ በኢትዮጵያ

**የሚጠበቁ ዝርዝር የመማር ውጤቶች**

- ኢትዮጲያዊያን ቀለምን በባህላዊ መንገድ እንዴት ያዘጋጁ እንደነበር፣ ለምን አገልግሎት እንደሚጠቀሙበት ታውቃላችሁ
- ጽሑፍ መጻፍና ሥዕል ለመሳል የሚጠቀሙትን ቀለማት ትለያላችሁ

የሀገራችን ሥዕል ታሪክ ጅማሬው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ላይ እንደሆነ ይነገራል፡፡ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ቀለምን የምትጠቀምባቸው ሁለት ዋና ነገሮችን ለማዘጋጀት ነው፡፡

1. ለጽሕፈት ዘዴ የቁም ጽሕፈት
2. ለሥነ-ሥዕል

1. **ለጽሕፈት ዘዴ የቁም ጽሕፈት፡-** ቤተክርስትያኗ ጥንትም ሆነ ዛሬ የምትገለገልባቸው ጠቃሚ የስነ ጽህፈት መሳሪያዎች አሏት፡፡ ይህም ጥበብ የቁም ጽህፈት ይባላል፡፡ የቁም ጽህፈት የሚገለጽበት የራሱ የሆነ የአሰራር ጥበብ አለው፡፡



ሥዕል.12 በጥቁርና ቀይ የተጻፈ የቁም ጽህፈትን

የቁም ጽህፈት ወይም ከሚጻፍበት ብራና አወጣጥ እስከ ቀለም ማዘጋጀት ድረስ ሊቃውቱ የሚጠቀሙበት የራሱ ጥበብ አሉት፡፡ ይህ የብራና ጽህፈት የሚጻፈው በጥቁር እና ቀይ ቀለም ነው፡፡

- **ጥቁር ቀለም፡-** ዋናውን ጽሁፍ ለመጻፍ ይጠቀሙበታል፡፡ ጥቁር ቀለም ለማዘጋጀት የተለያዩ ቅጠላ ቅጠሎችን አቃጥለው በማክሰል እንዲሁም ጥላሸት፣ የኩራዝ ጭስ እና ሌሎችንም ግብዓቶች ተጠቅመው ሂደቱን በመጠቀም ወደ ቀለምነት ይለውጡተል፡፡
- **ቀይ ቀለም፡-** የአምላካቸውን፣ የአማልእክትን ስም ለመጻፍ፣ ለምዕራፍ መግቢያ፣ ለነጥቦች ማስጌጫ፣ ለሀረግ መጣያ ይገለገሉበታል፡፡ ይህንንም ቀይ ቀለም ከአፈር፣ ከእንጆሪ ፍሬ፣ የተለያዩ ቀይ አበቦች እነዚህን እና ሌሎችንም ግባዓቶች ፈጭተው፣ ደቁሰውና አቡክተው ቀለሙን ያዘጋጃሉ፡፡

2 . **ለሥነ-ሥዕል**፡- ቤተክርስቲያኗ የራሷ የሆነ አሳሳልዘዴዎችና የምትጠቀምባቸው የቀለም አይነቶች አሏት፡፡የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያ ሥነ-ሥዕል ለመሳል ጥቁር፣ ነጭ፣ቢጫ፣ አረንጓዴ፣ቀይ እና ሰማያዊ ቀለማትን ብቻመጠቀማቸው ልዩ ከሚያደርጋቸው መገለጫዎች መካከልአንዱ ነው፡፡



*ሥዕል.13 ጥንታዊ ስዕል*

## መልመጃ አንድ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች እውነት ወይም ሐሰት በማለት መልሱ፡፡

1. ብራና ላይ በቀለም ፅሁፍ መፃፍ ይቻላል፡፡
2. ቀለም ከእፅዋት ማዘጋጀት አይቻልም፡፡

3. በድሮ ዘመን በብራና ላይ ፅሁፍ ለመጻፍ አረንጓዴ ቀለም ይጠቀሙ ነበር፡፡
4. የኖራ ድንጋይ ቀለም ይሰራበታል
5. በድሮ ጊዜ ስዕል ለመሳል ውስን ቀለማትን ብቻ ይጠቀሙ ነበር፡፡

### መልመጃ ሁለት

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ግለጹ፡፡

1 . መምህራችሁ በሚነግራችሁ መሰረት ከክፍል ጓደኞቻችው ጋር በቡድን እየሆናችሁ የለበሱትን ልብስ ግለፁጹ፡፡
2. መምህራችሁ በሚነግራችሁ መሰረት ቤተሰቦቻችሁ የለበሱትን ልብስ ቀለም ግለፁ፡፡

## 3.4.2 የሰንደቅ ዓለማ ትርጉም

**የሚጠበቁ ዝርዝር የመማር ውጤቶች**

- የሀገራችሁን ሰንደቅ አላማ ቀለም ትለያላችሁ ትስላላችሁ
- የሀገራችሁን ሰንደቅ አላማ ቀለም ትርጉም ታውቃላችሁ

## የሰንደቅ ዓላማ ቀለማት፤ ቅርፅና ትርጉም

**አረንጓዴው**፡- የኢትዮጵያ እድገትንና ልምላሜን ይወክላል።

**ቢጫው**፡- ተስፋ፣ፍትህና እኩልነትን ይወክላል።

**ቀዩ**፡- የህዝብ ነፃነት እኩልነት፣መስዋትነትንና ጀግንነትን ይወክላል።

**ኮከቡ**፡- የብሄር ብሄረሰቦችና የህዝቦች በእኩልነት ላይ የተመሰረተውን አንድነት ማሳያ ነው።

**ክብ የሆነው ሰማያዊ መደብ**፡- ሠላምን ያመለክታል። ቀጥታ እና እኩል በሆኑት መስመሮች መተላለፊያ ላይ የሚፈነጥቁት ቢጫ ጨረሮች በመፈቃቀድ ላይ የተመሰረተ አንድነት ለመሰረቱት ብሔረሰቦች የፈነጠቀውን ብሩህ ተስፋ ይጠቁማል።



*ስዕል.14 የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማው*

## መልመጃ ሶስት

ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ።

1. የኢትዮጵያ ሰንደቅ አላማ ላይ ስንት ቀለማት ይታያሉ?

ሀ/ አስር ለ/ አራት ሐ/ ሶስት መ/ መልስ የለውም

2. የባንዲራ ቀን መቼ ይከበራል?

ሀ/ በአመት አንድ ጊዜ ለ/ በየቀኑ ሐ/ በወር አንደ ጊዜ

መ/ በየሳምንቱ

3. ሠንደቅ ዓላማ ምንን ያመለክታል?

ሀ/ የሀገር መታወቂያ ምልክት ነው።

ለ/ የህዝብ አንድነት መጠበቂያ ምልክት ነው።

ሐ/ የክብር መለያ ምልክት ነው።

መ/ ሁሉም መልስ ናቸው።

### ማጠቃለያ

የክወናና የእይታ ጥበባት ባህላዊ እይታውን አውቃችኋል። ይህ ደግሞ የአንድን ሀገር ባህል እንድታውቁና እንድትረዱ ያደርጋችኋል። ሙዚቃ፤ ቲያትር ፣ እና የእይታ ጥበብ ባህልን ለማስተዋወቅ እንደሚረዱ ተገንዝባችኋል።

**ቀለም የሀገራችንን ባህል አጉልቶ በማሳየት በኩል ትልቅ ድርሻ ያለው ጥበብ መሆኑንም መረዳት አለባችሁ፡፡ በማንኛውም ስፍራ ላይ የምታዩትን ቀለማት ማስተዋል እና ከተፈጥሮ እና ከባህል ጋር ያለውን ትስስር ማጤን ይጠበቅባችኋል፡፡**

# ምዕራፍ 4

ምዕራፍ 4

## ሥነ-ውበታዊ እሴት (ዋጋ)

### መግቢያ

የሰው ልጆች በአካባቢያቸው የሚያዩትን ሰው ሰራሽም ይሁን የተፈጥሮ ክስተቶች መልካም እና ውብ ሆኖ ሲያገኙት ጥሩ ስሜት ይሰማቸዋል ጥሩ ስሜት መሰማት ብቻ ሳይሆን ያንን ያዩትን ነገር እንዲቆይ ወይም ተሻሽሎ እንዲቀመጥ ይመኛሉ:: የተሰማቸውንም ስሜት በተመቻቸው መንገድ ይገልጻሉ:: ይህም አድናቆት ይባላል:: አንድ ጥሩ ነገር ሲከወን ሰዎች ጥሩነቱን መግለጽ አለባቸው:: ተማሪዎችም ይህንን ስነምግባር ከወዲሁ እያዳበሩ ሊመጡ ይገባቸዋል::

ማድነቅ ማለት የተደረገውን ወይም የተከሰተውን ጥሩ ነገር እንዲቀጥል እና ዘላቂ እንዲሆን ማድረግ ማለት ነው

በዚህ ምዕራፍ በሚገኘው በክወናና በዕይታ ጥበባት ስር ልዩ ልዩ

ትምህርቶችን ትማራላችሁ::

የሙዚቃ ከያኒያን ማለት በአንድ የኪነጥበብ ስራ ውስጥ በመድረክ ላይ፤ በቴሌቭዥን፤በሬድዮ የሙዚቃ ስራቸውን የሚያቀርቡ ባለሙያዎች ናቸው::

# 2ኛ ክፍል



በኢትዮጵያ ሙዚቃ ታሪክ ውስጥ በዙ አስተዋፃ ያረጉ የሙዚቃ ከያኒዎች አሉ ከእነርሱ ውስጥም ስለጥቂቶቹ ትማራላችሁ።

እንዲሁም ደግሞ በሀገራችን በትወና ጥበብ የሚታወቁ ብዙ ከዋንያን አሉ። ነገር ግን በዚህ ክፍለ ትምህርት ሁሉንም ማንሳት አመቺ ስለማይሆን ለእናንተ ቅርብ የሆኑትን ጥቂት ከዋንያንን እናያለን።

በስተመጨረሻም በዚህ ክፍለ ትምህርት ተማሪዎች ሀገራችን ኢትዮጵያ ያፈራቻቸው የተለያዩ ሰዓሊያንን ትተዋወቃላችሁ። የስነ- ጥበብ ስራዎቻቸውም ትመለከታላችሁ፣ ታደንቃላችሁ።

**ከዚህ ምዕራፍ የሚጠበቅ የመማር ውጤት**

**ተማሪዎች በምዕራፉ ማጠቃለያ**

- የሙዚቃ ከዋኒዎችን ታደንቃላችሁ፤
- የዕይታ ጥበብ ከዋኒዎችን ታደንቃላችሁ።
- የትወና ተጫዋቾችን ታደንቃላችሁ፡

## 4.1 የሙዚቃ ከያኒዎችን ማድነቅ

**ከዚህ ርዕስ በኋላ የሚጠበቅ የመማር ውጤት**

- ከያኒዎች ማለት ምን ማለት እደሆነአ ትረዳላችሁ፡፡
- በኢትዮጵያ የሙዚቃ ከያኒዎችን ታውቃላቹሁ፡፡
- የምታውቁዋቸውን የሙዚቃ ከያኒዎችን ስማቸውን እና ስራቸውን ትናገራላችሁ፡፡

የሙዚቃ ከያኒዎች ማለት በአንድ የኪነጥበብ ስራ ውስጥ በመድረክ ላይ፤ በቴሌቭዝን፤በሬድዮ ስራቸውን የሚያቀርቡ ባለሞያዎች ናቸው፡፡

### 1 ማህሌት ቅዱስ ያሬድ

ያሬድ በኢትዮጵያ ሙዚቃ ታሪክ ውስጥ ከፍተኛ ቦታ ያለው ሰው ነው፡፡

ያሬድ በ 505 ዓ.ም በአክሱም አውራጃ ተወለደ፡፡ አባቱ ይሳቅ እና እናቱ ክርስቲና ይባሉ ነበር፡፡ ያሬድ በተወለደ በሰባት አመቱ አባቱ ስለሞተ እናቱ ክርስቲና ለአባቱ ወድም ለአጎቱ ለጌድዮን ተሰጠ፡፡ 25 አመት አስኪሞላው ድረስ አጎቱ ጋር አደገ፡፡ ከተማረ በኋላ የራሱን የፈጠራ ስራ እያስፋፋ ያሬድ ከፃፋቸው መፀሀፎች መሀል አንዱ ድጓ ነው፡፡

➢ ተማሪዎች ስለ ከያኒው ቅዱስ ያሬድ ከታላላቆቻችሁ ጠይቃችሁ በማምጣት በክፍላችሁ ውስጥ ያወቃችሁትን ከመምህራችሁ እና ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩ፡፡

## 2 ሙላቱ አስታጥቄ

ሙላቱ አስታጥቄ በኢትዮጵያ ሙዚቃ ታላቅ ዝና ያለውና የተለያዩ የሙዚቃ ስራዎችን በማቅረብ የታወቀ ሰው ነው፡፡ ከዚህም ሌላ በአለም አቀፍ ደረጃ ሊደመጡ የሚችሉ ሙዚቃዎችን በማቅረብ ሀገሩን እና ራሱን አስተዋውቋል፡፡ እዲሁም የማሪባ እና ኮንጋ የሙዚቃ መሳሪያ ተጫዋችም ነው፡፡ በኢትዮጵያ ጃዝ ሙዚቃ ከበርክሌ ዩኒቨርስቲ በሙዚቃ የክብር ዶክትሬት ማዕረግ አግኝቷል፡፡





➢ ተማሪዎች ስለ ከዋኙ ሙላቱ አስታጥቄ ከታላላቆቻችሁ ጠይቃችሁ በማምጣት በክፍላቹ ውስጥ ያወቃችሁትን ከመምህራችሁ እና ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩ፡፡

## 3 እጅጋየው ሽባባው

በጊዜው ከነበሩ የሴት ድምፃውያን አሁንም ካሉት ድምፃውያን ሁሌም እንደ አዲስ የምትደመጥ ድምፃዊት ናት፡፡እጅጋየው ልዩ ተሰጥኦ ያላት እና ዜማ እና ግጥም የመድረስ ችሎታዋ የሚደነቅ ባለሙያ ናት፡፡ በጊዜው ከነበረው ሙዚቃ ለየት ያለ ሙዚቃ ይዛ የመጣች ሙዚቀኛም ናት ፡፡




- ተማሪዎች ስለ ከያኒዋ እጅጋየው ሽባባው ከታላላቆቻችሁ ጠይቃችሁ በመምጣት በክፍላችሁ ውስጥ ያወቃችሁትን ከመምህራችሁ እና ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩ፡፡

### ሌሎች በኢትዮጵያ የሙዚቃ ጥበብ ውስጥ አሻራቸውን ያሳረፉ ከዋኒያን



አሊ ቢራ



ማሪቱ ለገሰ

አስናቀች ወርቁ





አስቴር አወቀ

ጥላሁን ገሰሰ



➢ እነዚህ ሙዚቀኞች ለኢትዩጵያ ሙዚቃ ትልቅ አሻራ ያሳረፉ ከዋንያን ናቸው፡፡

## መልመጃ

### የተማሪዎች ተሳትፎ

1. ተማሪዎች ከነዚህ ከያኒያን ውስጥ መርጣችሁ ስለ ስራቸው ከቤተሰቦቻችሁ ጠይቃችሁ በመምጣት በምን እዳደነቋቸው ትገልፃላችሁ፡፡

2. ተማሪዎች የምታውቋቸውን የምታደንቋቸውን የሙዚቃ ከያኒያንን ድርጊታቸውን ወይም ድምፃቸውን በክፍላችሁ ውስጥ በማስመሰል ከውኑ፡፡

## 4.2 የውዝዋዜ ከያኒያንን ማድነቅ

**ከዚህ ርዕስ በኋላ የሚጠበቅ የመማር ውጤት**

- በኢትዮጵያ የውዝዋዜ ከያኒዎችን ታውቃላችሁ::
- የምታውቋቸውን የውዝዋዜ ከያኒዎችን ስማቸውን እና ስራቸውን ትናገራላችሁ (ታቀርባላችሁ):
- አርኣያ ታገኛላችሁ

## እንዬ ታከለ



በሀገራችን የውዝዋዜ ስራ እጅግ በጣም ተወዳጅ የነበሩ እና አሁንም በጣም የሚወደዱ ተወዛዋዦች አሉ፤ ከእነርሱ መካከል የአገራችንን ስም በአለም ላይ እስከማስጠራት የደረሰችው አንዷ እንዬ ታከለ ናት::

# 2. ተመስገን መለሰ (ልጅ ተመስገን)



ተወዛዋዥ እና አሰልጣኝ ልጅ ተመስገን መለሰ፤ በውዝዋዜ ፍቅር የወደቀው ገና በለጋ እድሜው ነው፡፡ በቤተሰቡ ዘንድ በበዓላት ወቅት መጨፈር የተለመደ እንደነበር ያስታውሳል፡፡ ከቤቱ ውጭ ዳንስን መስራትና መለማመድ የጀመረው ተወልዶ ባደገበት ሽሮሜዳ እንደሆነ የሚናገረው ተመስገን፤ በ12 ዓመቱ በህፃናትና ወጣቶች ቲያትር ቤት ውስጥ ከሰፈሩ ልጆች ጋር የመሥራት እድል እንደገጠመው ያስታውሳል፡፡ ይኸም በሙያው እንዲገፋበት አድርጎታል፡፡

ልጅ ተመስገን መለሰ በተለያዩ መድረኮች የውዝዋዜ ተርዒት በማቅረብ የሚወደድ እና የሚደነቅ ከመሆኑም በላይ ከ 300 የማያንሱ ታዳጊዎችን በውዝዋዜ ሙያ አሰልጥኖ የተለያዩ መድረኮች ላይ ካሰለጠናቸው ልጆቹ ጋር ተርዒቶችን እየቀረበ ተወዳጅነትን አትርፎአል፡፡

# 2ኛ ክፍል

የክወናና የዕይታ ጥበባት ትምህርት



ምንጭ አዲስ አድማስ ጋዜጣ

Monday, 12 December 2016

## መልመጃ

➢ እንዬ ኢትዮጵያን በአለም ላይ ያስጠራችው በምንድን ነው?

## 4.3 የያትትር ክያኒያን ማድነቅ

**ከዚህ ርዕስ በኋላ የሚጠበቅ የመማር ውጤት**

ይህን ርዕስ ካጠናቀቃችሁ በኋላ የሚከተሉትን ትችላላችሁ

- የቲያትር ክያኒያንን ማድነቅ ትለምዳላችሁ
- ስለ ክያኒያኑ የተሰማችሁን አስተያየት መስጠትን ትለምዳላችሁ
- እናንተም ጥበባዊ እይታችሁን ከፍ ታደርጋላችሁ
- የቲያትር ሙያን ለመልመድ መንገድ ታገኛላችሁ

በዚህ ርዕስ ስር የምታዩአቸው ከያኒያን ስም ግለጹ

1. አርቲስት ተስፋዬ ሳህሉ (አባባ ተስፋዬ)
2. አርቲስት ንብረት ገላው (እከ)
3. አርቲስት ህብስት አሰፋ (ኪኪ) ጥሩምቤ ናቸው፡፡

## 1. አባባ ተስፋዬ (አርቲስት ተስፋዬ ሳህሉ)



አርቲስት ተስፋዬ ሳህሉ (አባባ ተስፋዬ)

በአዲስ አበባ ባህልና ቲያትር ውስጥ በተዋናይነት፤ የተለያዩ ተውኔቶችን ተጫውተዋል፡፡ የሴት ገጸ ባህሪ ተላብሰውም ይጫወቱ ነበር፡፡

- መድረክ መሪ፣

- ተዋናይ፣
- ሙዚቀኛ
- ትርኢት አቅራቢ፣
- ድምፃዊ፣
- የሙዚቃ መሳሪያ ተጫዋች፣
- የውዝዋዜ አሰልጣኝ፣
- የቴሌቪዥን ፕሮግራም አዘጋጅ፣
- ደራሲና ተረት ነጋሪ (የተረት አባት) ነበሩ

አባባ ተስፋዬ ለረጅም አመታት በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን የልጆች ፕሮግራም ላይ ልጆችን በመምከር፣ በማጫወት እና ብዙ ተረቶችን ለልጆች በማውራት የሚታወቁ ሲሆን አባባ ተስፋዬን የማይወዳቸው ልጅ አልነበረም፡፡ ሁሉም ይወዳቸው ነበር፡፡ከዚህም የተነሳ የልጆች አባት እየተባሉ ይጠሩ ነበረ፡፡

**አባባ ተስፋዬ የሚታወቁበት ደስ የሚለው ንግግራቸው፡-**

**ጤና ይስጥልኝ ልጆች የዛሬ አበባዎች የነገ ፍሬዎች እንደምን አላችሁ ልጆች አያችሁ ልጆች የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን የልጆች ክፍለ ጊዜ ዝግጅት እናንተን ለማስደሰት ልክ በሰአቱ ይገኛል፡፡ አባባ ደግሞ የልጆች ሰአት እንዳያልፍባቸው በሩጫ ዲ ዲ ዲ እያሉ ከተፍ፡፡ እናንተ ደግሞ አባባ ይመጣሉ ብላችሁ ቆማችሁ ትጠብቃላችሁ፡፡ በጣም ጥሩ ነው ልጆች፡፡ አባት ሲመጣ በአክብሮት መነሳት አስፈላጊ ነው ............**

## መልመጃ አንድ

- አባባ ተስፋዬ የሚታወቁበት ሙያቸው ምንድነው?

## 2 ንብረት ገላው (እከ)



## ንብረት ገላው (እከ)

- የተለያዩ የሬዲዮና የቴሌቪዥን ድራማዎች ላይ ተሳትፏል
- የልጆች ፕሮገራም ላይ ከ አባባ ተስፋዬ ጋር ሰርቷል
- በ ኢትዮጵያ ቴሌቪዥን መዝናኛ ላይ **ነቅዕ** የተሰኘው ድራማ አዘጋጅ ነው።



**እከ**

ተወዳጅ በሆነው የቤቶች ድራማ ላይ በጣም እንቅልፋም ጥበቃ ሆኖ የሚሰራ ኀበዝ እና የሚያስቅ ተዋናይ ነው።

**እከ**

**በቤቶች ድራማ ላይ እኔን ነው........እና እከደከን ማን ችሎት በጎልበትም ሆነ በብልጠት ሁሌም ከወንድ በላይ አበጀ.....በሚለው አስቂኝ አነጋገሩ የማይረሳ ተወዳጅ ገጸባህሪ ነው**

## መልመጃ ሁለት

### ትክክለኛውን መልስ ባጭሩ መልሱ

1. እከ እንቅልፋም ሆኖ የሚሰራበት ድራማ ምን ይባላል

**3.ህብስት አሰፋ (ጥሩምባ)**



የኢትየጵያ ልጆች ቴሌቪዥን ላይ የምናውቃት በልጆች የምትወደድ ከያኒ ናት። የትወና ጨዋታ የጀመረችው ገና ከልጅነቷ ነው። ከምንም ነገር የበለጠ ለልጆች ትልቅ ፍቅር አላት በዚህ የተነሳ በጣም ብዙ የህጻናት ቲያትሮችን አዘጋጅታለች

በአሁኑ ጊዜ ደግሞ የኢትዮጵያ ልጆች ቴሌቪዥን ላይ

- ከልጆች ጋር ትጫወታለች.
- ትደንሳለች
- ትዘፍናለች

በተለይ ከሁሉም በላይ የሚገርመው እና ደስ የሚለው ችሎታዋ፡- እንደ ህጻን ልጅ ስታወራ የእውነት ህጻን ነው የምትመስለው፡፡

## መልመጃ ሶስት

ትክክል የሆነውን እውነት ትክክል ያልሆነውን ደግሞ ሀሰት በማለት መልሱ

1 ህብስት አሰፋ ልጆችን ትወዳለች

## 4.4 የእይታ ጥበብ ከያኒያንን ማድነቅ

### መግቢያ

በዚህ ክፍለ ትምህርት ተማሪዎች ሀገራችን ኢትዮጵያ ያፈራቻቸውን የተለያዩ ሠዓሊያንን እንተዋወቃለን፡፡ የስነ- ጥበብ ስራዎቻቸውንም እንመለከታለን፣ እናደንቃለን፡፡

**የሚጠበቁ ዝርዝር የመማር ውጤቶች**

**ከዚህ ትምህርት በኋላ:**

- ሀገራችን ከሚገኙ የእይታ ጥበብ ባለሙያዎች ከያኒያንና ስራዎቻቸውን ታደንቃላችሁ፡፡
- አይታችሁ የወደዳችሁትን ወይም ያደነቃችሁትን የሠዓሊውን ፎቶግራፍ ወይም ሠዓሊው የሰራውን መሳል ትለማመዳላችሁ፡፡

## ማድነቅ

በሀገራችን ጥቂት የማይባሉ አንጋፋና ታዋቂ ሰዓሊያንና ቀራፂያን ይገኛሉ። ሠዓሊያን ሥዕል ለመሳል ቀለም፣ ብሩሽ፣ ሸራ፣ ወረቀት እና ሌሎችንም መሳያ ቁሰቀቁሶችን በመጠቀም የስዕል ስራቸውን ይሰራሉ። ቀራፂያን ደግሞ ቅርፃ-ቅርፅ ለመስራት ጭቃ (አፈር)፣ ብረት፣ ጀሶ፣ ሲሚንቶ እና የመሳሰሉትን ይጠቀማሉ። እነዚህንና ሌሎች ግብአቶች በመጠቀም ድንቅ የሆኑ የጥበብ ስራዎቻቸውን ይሰራሉ። ከነዚህ የሥነ-ጥበብ ባለሙያዎች መካከል የጥቂቶቹን እንመልከት፡-

1. **ሠዓሊ ወሰኔ ወርቄ ኮስሮፍ፡-** የቀለም ቅብ ስራና የቅርፃ-ቅርፅ ስራዎችን በመስራትና በስራዎቹም የኢትዮጵያን ፊደላትን በመጠቀም ይታወቃል።



*ሥዕል.15 ሠዓሊ ወሰኔ ወርቄ ኮስሮፍ የቀለም ቅብ ስራ*

2. **ሠዓሊ ወርቁ ማሞ፡-** የሥነ-ጥበብ ትምህርታቸውን በአዲስ አበባ ሥነ-ጥበብ ትምህርት ቤት እንዲሁም በውጪ ሀገር የቀለም ቅብ ትምህርት ተከታትለዋል። በሀገር ውስጥና ከሀገር ውጪ የተለያዩ አውደ ርዕዮች ላይ ተካፍሏል። ከሰዓሊው የቀለም ቅብ ስራዎች መካከል፡-





ሥዕል.16 ሰዓሊወርቁ ማሞ እና የቀለም ቅብ ስራቸው

3 . **ሠዓሊ (ቀራፂ) ታደሰ በላይነህ፡-** ኢትዮጵያ ካፈራቻቸው ጥቂት ቀራፂያን መካከል አንዱ ሲሆኑ በአለ የስነጥበብና ዲዛይን ትምህርት ቤት በመምህርነትና በዳይሬክተርነት አገልግለዋል።

 

ሠዓሊ3 (ቀራፂ) ታደሰ በላይነህ እና የቅርጻ ቅርጽ ስራቸው

## መልመጃ አንድ

### ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ስጡ፡፡

1. የሥዕል ስራዎቹ ላይ የአማርኛ ፊደላትን በመጠቀም የሚታወቀው ሠዓሊና ቀራፂ ስሙ ማን ይባላል፡፡

ሀ. ሠዓሊ (ቀራፂ) ታደሰ በላይነህ

ለ. ሠዓሊና ቀራፂ ወሰኔ ወርቄ ኮስሮፍ

ሐ. ሠዓሊ ወርቁ ማሞ

መ. ሠዓሊ ለማ ጉያ

## መልመጃ ሁለት

የተለያዩ ሠዓሊዎችንና የሥዕል ስራዎች ተመልክታችሁ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ተግባራዊ አድርጉ፡፡

1. የሥዕል ስራዎች በማየት ያደንቁትን ሥዕል ይስላሉ፡፡
2. የምታደንቁትን ሠዓሊ ፎቶግራፍ ሳሉ፡፡
3. ሥዕሎቹን በምን ምን እንዳደነቃችሁ ለመምህራችሁ ግለፁ፡፡

## ማጠቃለያ

ከያኒያንን ማወቃችሁ ሁለት ትርጉም ይኖረዋል፡፡ አንደኛው ታላላቅ ከያኒያንን የማድነቅ ባህልን ከወዲሁ እያዳበራችሁ ትመጣለቹ፡፡ ሌላው ተማሪዎች የራሳችሁን ዝንባሌ እንዴት አድርጋችሁ ማሳደግ እደምትችሉ መንገድ እድታገኙ ይረዳችኋል፡፡በሃገራችን በትወና ጨዋታቸው የሚታወቁት በዚህክፍለትምህርት ውስጥ የተጠቀሱት ብቻ አይደሉም፡፡ በዚህ አስደሳች ሙያ ውስጥ በጣም ብዙ ሰዎች አሉ፤ ስለዚህ ሌሎች የምታውቋቸውን እያስታወሳችሁ እናንተም እንደነሱ ጎበዝ የትወና ተጫዋች መሆን የምትችሉበትን ሁኔታ ከወዲሁ ማዘጋጀት ይኖርባችኋል፡፡

በሙዚቃና በተውኔት ብቻ ሳይሆን በሀገራችን ኢትዮጵያ ብዙየእይታ ጥበብ ባለሙያዎች አሉ፡፡ በዚህ ትምህርት ክፍል ውስጥየተጠቀሱት በጣም ጥቂቶቹ ሲሆኑ፤ስለ ኢትዮጵያ ጥበብ የተፃፉጽሑፎችን በማንበብና በመመልከት ከዚህ በበለጠና በተሻለስለሀገራችን ሠዓሊያንና ቀራጺያንን ማወቅና ማድነቅ ተገቢ ነው፡፡

## የማጠቃለያ መልመጃዎች (ምዘና)

### ትክክለኛውን መልስ በመስጥት ባዶ ቦታዎችን ሙሉ

1. የሙዚቃ ከያኒያን በአንድ የኪነጥበብ ስራ ውስጥ

የ___________________ ስራ የሚያቀርቡ ባለሞያዎች ናቸው።

2 . ያሬድ በ_______ በአክሱም አውራጃ ተወለደ።

3. ያሬድ አባቱ _____ እና እናቱ _____ ይባሉ ነበር።

4. እጅጋየው ልዩ ተስጥዖ ያላት____________ የመድረስ

ችሎታዋ የምትደነቅ ባለሞያ ናት።

5. ያሬድ ከፃፋቸው መፀሀፎች መሀል አንዱ _____ ነው።

### የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባጭሩ መልሱ

1. አርቲስት ተስፋዬ ሳህሉ (አባባ ተስፋዬ) የልጆች አባት የተባሉት ለምንድነው?
2. የጥሩምቤ ትክክለኛ ስሟ ማነው?
3. እናኑ ታከለ ተወዳጅ ያደረጋት ምንድን ነው?

### ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ።

2. ሠዓሊያን ይስላሉ።

ሀ. ጽሁፍ ለ. ሥዕል ሐ. ግጥም

3. ታደሰ በላይነህ የ__________________ ባለሙያ ናቸው።

ሀ. የሙዚቃ    ለ. የቲያትር

ሐ. የቅርፃ-ቅርፅ    መ. መልሱ አልተሰጠም

# ምዕራፍ 5

## ጥመርታ ዝምድናና ትግበራ

### መግቢያ

የክወናና የእይታ ጥበባት ለልጆች የሚቀርቡ የእውነት፣ እና የፍቅር ስሜት መግለጫ መንገዶች መሆናቸውን ማወቅ አለባችሁ፡፡ለእናንተ ለተማሪዎች የትምህርት አቀባበል ስርዓት፤ ለአእምሮአችሁ እድገት በጣም ጠቃሚ ነው፡፡ በእያንዳንዱ የትምህርት ክፍለ ጊዜ ለተማሪዎች ጥበባዊ በሆነ መንገድ ትምህርት መስጠት አስፈላጊ ነው፡፡

የተማሪዎችን የመቀበል ሂደት ውጤታማ ያደርጋል፡፡

ጥበብ በማንኛውም መስክ አብሮ የሚኖር መሆኑን ማሳያ ነው፡፡

**ከዚህ ምዕራፍ መጠናቀቅ በኋላ የሚጠበቅ የመማር ውጤት**

- የክወና እና ዕይታ ጥበብ ዘርፍ ከሌላው ትምህርት ጋር ያለውን ዝምድና ትለያላችሁ
- የክወና እና የዕይታ ጥበብ ከሌላው ትምህርት ጋር ያለውን ጥቅም ትለያላችሁ
- በክወና እና በዕይታ ጥበባት መካከል ያለውን ትስስር ትረዳላችሁ

## 5.1 የሙዚቃ ተግባራት

**ከዚህ ርዕስ በኋላ የሚጠበቅ የመማር ውጤት**

- ➢ ሙዚቃ ምን አይነት ተግባሮችን እደሚሰጥ ታዉቃላችሁ፡
- ➢ ሙዚቃ ከውዝዋዜ ጋር ያለውን ተግባራት ታውቃላችሁ፡

- ሙዚቃ አምሮን የተሻለ ያደርጋል፡፡ ሰዎች ሙዚቃ በሚሰሙበት ጊዜ አእምሮዋቸውን ማረጋጋት እና የተሻለ እዲሰራ ያደርጋል፡፡

**መዝሙር አንድ** ፡-ዥው ዥው

ወዲያ ወዲይ ዥው ዥው

ወዲያ ወዲይ ዥው ዥው

ያስደስታል መጫወት

በህበረት ሆኖ በአድነት

ወዲያ ወዲይ ኸው ኸው

ወዲያ ወዲይ ኸው ኸው

እስኪበቃን መጫወት ነው

ኸዋ ኸዌ ኸው ኸው

**ግጥም ዜማ፡-** ውቤ ካሴ

## የመዝሙሩ አላማ

በህብረት ሆናችሁ መጫወት እና ጫዋታ ለህፃናት

እደሚያስደስትየሚያሳይ ነው።

- ሙዚቃ ለአካቶ ትምህርትይጠቅማል።አካል

ጉዳተኞችሙዚቃዎችን በሚጫወቱበት ጊዜወይም

በሚሰሙበት ጊዜከሌሎች ጋር ያላቸው መግባባት እና

ተሳትፎዋቸውንይጨምራል።

- ሙዚቃ የተለያዩህክምናዎችን ይሰጣል።

የተለያዩህሙማንን ህመማቸውንበሙዚቃ ማከም ይቻላል።

የተያዩፊዚዮ ቴራፒዎች በሙዚቃውስጥ በመስጠት  የአካል

እና የአይምሮ ህክምናዎች ማድረግይቻላል።

**መዝሙር ሁለት፡-** አዲስ አበባ

አዲስ አበባ አዲስ አበባ
አዲስ አበባ አዲስ አበባ
አዲስ አበባ አዲስ አበባ
አዲስ አበባ አዲስ አበባ
አዲስ አበባ አዲስ አበባ
የአፈሪካ አድነት አምባ
አሀጉር አቀፍ ታሪክ የሚከወንብሽ
ሀገር አቀፍ ስራ የሚሰራብሽ
ዋና ከተማችን አዲስ አበባ ነሽ
አዲስ አበባ ነሽ
በጣም ደስ ይለናል ስንዘምርልሽ
አዲስ አበባችን የኛ ነሽ የኛ ነሽ

ግጥም ፡- መምህር ፈታሁን

ቅንብር፡- በስራት ታመነ

- ልዩ ልዩ የድምፅ ቅንበሮች የሙዚቃ ውጤቶች ናቸው፡፡ ህፃናቶችም ሙዚቃን በሚሰሙበት ጊዜ አፋቸውን ቶሎ ለመፍታት እና ካሉበት ማህበረሰብ ጋር የተለያዩ ተሳትፎ እና መግባባትን ቶሎ ይፈጥራሉ፡፡

- ሙዚቃ የቋንቋ ክህሎትን ይጭምራል። ህፃናቶች ሙዚቃን በሚሰሙበት እና የሰሙትንም በሚዘምሩበት ጊዜ የድምፅ አውታራቸውን ይጨምርላቸዋል።
- ሙዚቃ በምንሰማበት ፤ ጊዜ የተለያዩ እንቅስቃሴዎች እዲፈጠሩ በማድረግ ሙዚቃ ትልቁን ድረሻ ይወስዳል።

**መልመጃ አንድ**

**ትክክል የሆነውን እውነት ስህተት የሆነው ሀሰት በማለት መልሱ።**

1 . ሙዚቃ አእምሮን የታሻለ ያደርጋል።

2 . የዥው ዥውን ግጥም እና ዜማ የውቤ ካሳውን አይደለም።

3 . ሙዚቃ ለአካቶ ትምህርት ይጠቅማል።

4 . የተለያዩ ህሙማንን ህመማቸውን በሙዚቃ ማከም ይቻላል፡

## 5.1.1 ሙዚቃ ሌሎች የትምህርት አይነቶች ያለው አስተዋፅኦ

ከዚህ ርዕስ በኂላ የሚጠበቅ የመማር ውጤት

- ሙዚቃ ከሂሳብ ትምህርት ጋር ወይም ከቁጥር ጋር ያለውን ዝምድና ታውቃላቹችሁ።

ሙዚቃ ከቁጥር ጋር የሚያቆራኝ ትምህርት ነው።

ይህ የቁጥር ትምህርትም የሚገኘው በሒሳብ ትምህርት ውስጥ ነው።

ኖታዎች ብዙን ጊዜ ሲቆጠሩ እንደ ኖታዎ ቹ የተለያዩ የቁጥር መጠን አላቸው፡፡ በቁጥር ኖታዎችንም እየቆጠርን ስንት እንደሆኑ ማወቅ ይቻላል፡፡



ሁለቱ ኖታዎች ሁለት ሁለት ምት አላቸው ሁለቱ አንድ ላይ አራት ምት የጊዜ ቆይታ ይሰጣሉ፡፡

## መልመጃ ሁለት

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዶ ቦታዎቹን ሙሉ**

1 ሙዚቃ______ የሚያቆራኝ ትምህርት ነው፡፡

2 የሙዚቃ ቁጥር ትምህርት ውስጥ ወደሚገኘው______ ውስጥ ነው፡፡

## 5.1.2 ውዝዋዜ ለሌሎች የትምህርት አይነቶች ያለው አስተዋፅኦ

**ከዚህ ርዕስ መጠናቀቅ በኋላ የሚጠበቅ የመማር ውጤት**

- ውዝዋዜ ያለውን ጥቅም ትረዳላችሁ
- ውዝዋዜ ለሌሎች ትምህርቶች ያለውን አስተዋጽኦ ትረዳላችሁ

➢ ውዝዋዜ የሰውነት እና የአእምሮ ስራ ነው። ሰዎች እንቅስቃሴ በሚያደርጉበት ጊዜ ከአካላዊ ቅልጥፍና ባሻገር አእምሮአቸው ነገሮችን የማስተዋል ብቃት ይኖረዋል።

ዘውትር የሚንቀሳቀስ ተማሪ ሰውነቱና አእምሮው የተፍታታ ስለሚሆን ትምህርቱን በአግባቡ ለመከታተል ዝግጁ ይሆናል

## 5.1.3 ቲያትር ለሌሎች የትምህርት አይነቶች ያለው አስተዋፅኦ

**ከዚህ ርዕስ መጠናቀቅ በኋላ የሚጠበቅ የመማር ውጤት**

- ቲያትር ለሌሎች የትምህርት አይነቶች ያለውን አስተዋፅኦ ታውቃላችሁ
- ንቃተ ህሊናችሁ ይዳብራል
- የመማር ፍላጎታችሁ ከፍ ይላል

የቲያትር ጥበብ በሁሉም የሰው ልጆች እነቅስቃሴ ውስጥ ይገባል። አኗኗርን፣ስራን፣ትምህርትን ወዘተ ይመረምራል። ሁሉንም የሰው ልጆች ጉዳዮች ያነሳል። ለዚህ ነው ቲያትር ለሌሎች የትምህርት አይነቶች አስተዋፅኦ ያለው።

- **የቲያትር ትምህርት**

1.የቲያትር ትምህርት ምንድነው?

2.የቲያትር ትምህርት ለምን ይጠቅማል?

የእነዚህን ጥያቄ መልሶች ለመመህራችሁ አስረዱ

**ተውኔት**

- ✓ ተውኔት እንደሌሎች ጥበባት ሁሉ ያዝናናል ያስተምራል፣ ይመከራል፡፡
- ✓ ተወኔት ውስጥ የተለያዩ የትምህርት አይነቶች በተለያየ መንገድ ይካተታሉ፡፡

**ምሳሌ**

ይህንን ተውኔት በየተራ ከሰራችሁ በኋላ የሚሰጣችሁን ትምህርት አጢኑት

❖ አቡሽ ጌም እየተጫወተ ነው፡፡ እህቱ ትመጣለች

ተውኔት 1

እህት፡- አቡሽ ምን እያደረክ ነው

አቡሽ፡- እየተጫወትኩ

እህት፡- ፈተና ደርሷል እኮ አታጠናም እንዴ

አቡሽ፡- በደንብ አጠናሁ እኮ

እህት፡- እስቲ ልጠይቅህ

አቡሽ፡- ጠይቂኛ

እህት፡- እሺ በ B የሚጀምር ቃል ምንድነው

አቡሽ፡- በ B የሚጀምር ቃል B እ እ እ እ B እ እ እ እ

DOG

እህት፡- ቂ ቂ ቂ ቂ BOOK ነው ወይም BAG

አቡሽ፡- ወይኔ ተሸወድኩ

እህት፡- እሺ በ F የሚጀምርስ ቃል ምንድነው

አቡሽ፡- F F F እ እ እ እ ቆይ አትንገሪኝ አዎ ፈረስ

እህት፡- ቂ ቂ ቂ FOOD ነው ወይም FATHER

አቡሽ፡- በቃ እንደውም አልማርም

ተፈጸመ ከ በሀይሉ ዘለቀ 2013

ተውኔቱ በአንድ በኩል ያዝናናል በሌላ በኩል ደግሞ የ እንግሊዝኛ ቋንቋን ያስተምራል፡፡

## መልመጃ 1

## ተውኔት 2

ከስር ያለውን ተውኔት ከሰራችሁ በኂላ ምን እንደተማራችሁበት ለመምህራችሁ አስረዱ

ቤቲ፡- መፅሐፍ ታነባለች ሚኪ ደሞ በፍርሃት እየሮጠ ይገባል

ቤቲ፡- ወይኔ ጉዴ ምን ሆነህ ነው

ሚኪ፡- ጉዳችን ፈላ ሰፈራችን ውስጥ አንበሳ መጣ

ቤቲ፡- ወይኔ እናቴ ድረሽ የት አየኸው

ሚኪ፡- እዚ እኛ በር ጋ ቁጭ ብሎ

ቤቲ፡- እ እ እ ምን እናድርግ ጉዳችን ነው ዛሬ

ሚኪ፡- እኔንጃ ወይኔ አባይ ድረስልን

አባት፡- ምን ሆናችሁ

ቤቲ፡- አንበሳ ሰፈራችን መጣ

አባት፡- የት አየሽው

ቤቲ፡- እሱ ነው ያየው እኔ አይደለሁም

አባት፡- አትፍሩ አንበሳ የዱር እንስሳ ነው እዚ አይመጣም

ሚኪ፡- እቺ ፈሪ

ቤቲ፡- አንተ ነህ ፈሪ

ሚኪ፡- አረ አንቺ ነሽ ፈሪ

አባት፡- ሁለታችሁም አትፍሩ አሁን ወደ ጥናት

ተፈጸመ ከበሀይሉ ዘለቀ 2013

ከድራማው የተረዳችሁትን ለመመህራችሁ አስረዱ

## 5.1.4 ዕይታ ጥበብ ለሌሎች ትምህርት ዓይነቶች ያለውን አስተዋጽኦ መግለፅ

### መግቢያ

በዚህ ክፍለ ትምህር ክፍል ተማሪዎች የዕይታ ጥበብ መማራቸው በአካዳሚያዊ ስኬት ላይ የሚያሳድረው አዎንታዊ ተፅእኖ በራሱ ዋጋ ቢኖረውም ፣ መላውን የሰው ልጅ የመማር ስልትን የበለጠ ስኬታማ በማድረግ ተማሪዎችን ከመፍጠር ባሻገር የተሻለ የትምህርት አቀባበል እንዲኖራቸው ያደርጋል ፡፡

**ከዚህ ርዕስ መጠናቀቅ በኂላ የሚጠበቅ የመማር ውጤት**

የክወናና ዕይታ ጥበብን መማራችው ለሌሎች ትምህርት ዓይነቶች ያለውን አስተዋጽኦ ትገልጻላችሁ

በስርአተ ትምህር ውስጥ የስነ ጥበብ ትምህርት እጅግ አስፈላጊ ነው። ሥነ ጥበብ በአካዳሚያዊ ስኬት ላይ የሚያሳድረው አዎንታዊ ተፅእኖ በራሱ ዋጋ ቢኖረውም ፣ መላውን የሰው ልጅ የመማር ስልትን የበለጠ ስኬታማ በማድረግ ተማሪዎችን ከመፍጠር ባሻገር የተሻለ የትምህርት አቀባበል እንዲኖራቸው ያደርጋል ፡፡

የስነ ጥበብ ትምህርትን በመማር የመጀመሪያ ደረጃዎች ውስጥ ተማሪዎች አስደሳች (ውስጣዊ ተነሳሽነት) እንዲኖራቸው ከፍተኛ አስተዋፅኦ ይፈጥርላቸዋል። ይህ ዓይነቱ ተሳትፎ ተማሪዎችዎ በትምህርታቸው እንዲያድጉ እና እንዲሻሻሉ ይረዳቸዋል።

አሜሪካውያን ለሥነ -ጥበብ ትምህርት ባቀረቡት ጥናት መሰረት ስነ ጥበብን በቀን ለሶስት ሰዓት በሳምንት ለሶስት ቀን ለአንድ ዓመት የተማሩ ልጆች በሳይንስ፣ በሒሳብ፣ በድርሰትና በግጥም ስነ ጥበብን ካልተማሩ ልጆች የተሻለ ውጤት ማስመዝገባቸውን አረጋግጠዋል።

እንደ አውሮፓውያን የዘመን አቆጣተር በ2010 በሚዙሪ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ላይ በተደረገ ጥናት ስነ ጥበብን የተማሩ ልጆች በከፍተኛ መጠን የዲሲፕሊን ጥሰቶችን ቀንሰው በሰዓታቸው የሚገኙ ሆነው ተገኝተዋል።

ስነ ጥበብ፤ ለተማሪዎች ግልጽ የሆኑ ግቦችን እና መርሆዎችን በማስቀመጥ እና ከዚያ በተከናወነው ሥራ እና በውጤቶቹ መካከል ያለውን ትስስር በመሳል፣ ተማሪዎች ተነሳሽነታቸውን መለወጥ መጀመር ይችላሉ፣ ይህም በጣም ጤናማ እና ዘላቂ የመማር ሂደትን ለመፍጠር ያግዛል።

የስነ-ጥበብ ትምህርትን መማራቸው ሌሎች የትምህርት አይነቶችን ያሚያደርገው አስተዋፅኦ፡-

- ለችግሮች መፍትሔ ይሰጣል፡፡ ለምሳሌ በመማር ማስተማር ሒደት ውስጥ ለመግለጽ ወይም ለማስረዳት አስቸጋሪ የሆኑ ጽንሰ -ሀሳቦችን ስዕል የበለጠ ለማስረዳትና ለመረዳት ቀላል ያደርጋቸዋል፡፡
- የተማሪዎችን የአእምሮና የአካል ወይም የእጅን በጥምረት ተቀናጅተው የመስራት ችሎታን እንዲያዳብሩ ይረዳል፣
- የማሰተዋል ወይም የማስታወስ አቅማቸው እንዲጨምሩና እንዲያዳብሩ ያግዛቸዋል፣ ለታሪካቸውና ለባህላችው ያላቸውን አመለካከትና ግንዛብ ይጨምርላቸዋል፣
  - የመመራመርና ፍላጎታቸውን ለማዳበር ያግዛቸዋል፣
  - ራሳቸውን በፈጠራ እንዲያሳደጉ ይረዳቸዋል፡፡

ተማሪዎችን በሥነ-ጥበብ ትምህርት ውስጥ ማሳተፍ ብዙ ርዕሰ ጉዳዮችን እንዲዳስሱ ያደርጋቸዋል፡፡

ለምሳሌ በስነ-ጥበብ ትምህርት ውስጥ፡-

- የሰው ወይም የእንስሳትን ምስል ሲስሉ -እግረመንገዳቸውን የሰውነት ክፍሎቻቸውን፣ የስሜት ህዋሶቻቸውን፣

- በመልክዓ ምድር ስዕል - ስለ መሬት (የመልክዓ ምድር) አቀማመጥ ማድነቅ፣ የተክሎችን ተፈጥሮን፣ጥቅም ማወቅ መለየት ወዘተ...ያሰችላቸዋል።
- የሰውነት ክፍሎች መጠን አንዱን ከአንዱ ለማወቅ በሂሳብ ስሌት ይከፋፋፍለዋል። ለምሳሌ:-







## መልመጃ አንድ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች እውነት ወይም ሐሰት በማለት መልሱ፨

1. የስነ ጥበብ ትምህርት እጅግ አስፈላጊ ነው።
2. ስነ-ጥበብ ተማሪዎች ራሳቸውን በፈጠራ እንዲያሳድጉ ያግዛቸዋል።
3. ስዕል ሀሳቦችን የበለጠ ለማስረዳትና ለመረዳት ያቀላል።

## 5.2 በክወና እና በዕይታ ጥበባት መካከል ያለውን ዝምድና መለየት

**ከዚህ ርዕስ በኋላ የሚጠበቅ የመማር ውጤት**

- በክወና እና በዕይታ ጥበባት መካከል ያለውን ዝምድና ትለያላችሁ
- በክወና እና በዕይታ ጥበባት መካከል ያለውን ልዩነት ትረዳላችሁ

### • የክወና እና የዕይታ ጥበባት

የክወና እና የዕይታ ጥበባት ማለት በድርጊት ወይም በክዋኔ የሚቀርብ የጥበብ ስራ እና በምስል የሚቀርብ ጥበብ ማለት ነው።

ልዩነታቸው፡-

- በድርጊት ወይም በክዋኔ የሚቀርቡ የጥበብ ስራዎች የሚባሉት ሙዚቃ፣ውዝዋዜ፣ቲያትር፣ ፊልም ሲሆኑ
- በዕይታ የሚቀርቡ የጥበብ ስራዎች ደግሞ ፎቶገራፍ፣ ሥዕል፣ቅርጻቅርጾች ናቸው።

ዝምድናቸው፡-

የጥበባት ስራ መሆናቸው፣በፈጠራና በክህሎት የሚሰሩ መሆናቸው፣ከሰዎች የዕለት ዕለት አኗኗር የሚቀዱ መሆናቸው አንድ ያደርጋቸዋል፡

# 2ኛ ክፍል



## ማጠቃለያ

የክወና እና ዕይታ ጥበብ ስለ ብዙ ነገሮች ስለሚያስረዳ ከሂወታችን ጋር የተያያዘ ነው ሊባል ይችላል። ስለዚህ ተማሪዎችም  ሙዚቃ በሚሰሙበትም ይሁን በሚጫወቱበትጊዜ አካላዊና ስነልቦናዊ ሂወታቸው የተረጋጋ ይሆናል። ሙዚቃከቁጥር ጋር ያለውን ቁርኝት ተማሪዎች ማወቃቸው የቁጥር ድምር ቁጥሮችን የመደመር ክህሎታችሁ ይጨምራል። እንዲሁም ደግሞ ተውኔት ስለ ብዙ ነገሮች ስለሚያስረዳ ከሂወታችን ጋር የተያያዘ ነው ሊባል ይችላል። ስለዚህእናንተም ተውኔት በምታዩበት ወይም በምትሰሩበት ጊዜበውስጡ የያዘውን ሃሳብ እና ትምህርት በደንብ ማስተዋልአለባችሁ።የስነ-ጥበብ ትምህርትም ሌሎች የትምህርት አይነቶችን በቀላሉእንዲረዱ ያግዛቸዋል የአሰተሳሰብ አድማሳቸውንም ያሰፋል።

## ዋቢ መጽሀፎች

1. ግሩም ኤርሚያስ ወጋየሁ፤ መሰረታዊ የትወና መማሪያ (ትርጉም)፤ የመጀመሪያ ህትመት፤ 2001
2. ዐረፈ ዐይኔ ሐጎስ፡- አለቃ ገ/ሃና እና አስቂኝ ቀልዶቻቸው
3. ከበደ ሚካኤል፡- ታሪክና ምሳሌ 2ኛ መፅሐፍ፤ሜጋ አሳታሚ፤1999
4. ፋንታሁን እንግዳ፡፡ ሰነ ጹሁፋዊ ሙዳዬ ቃላት ከነ ማብራሪያቸው፡
፡ አርቲስቲክ ማተሚያ፡ 2003፤ አዲስ አበባ፡፡
5. ልዩ ልዩ ጨዋታዎች፡፡ በስርአተ ትምህረት ሱፐርቪዥን መምሪያ፤
ት/ሚኒስቴር 1968፡፡
6. የ 8ኛ ክፍል የስነጥበብ መማሪያ፡፡ ሚያዚያ 2009
7. ቀሲስ ከፍያለው መራሒ፡፡ የቤተክርስቲያን አስተዋጽኦ ለኢትዮጵያ
ስልጣኔ፤ የካቲት 1986
8. የሰንደቅ ዓላማ ትርጉም፡፡ የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፤ ጥቅምት 2008
9. ተስፋዬ ለማ፡፡ የኢትዮጵያ የሙዚቃ ታሪክ፤ 2005
10.https://www.bbc.com> amharic November 28, 2017

የክወናና የዕይታ

ጥበባት ትምህርት

አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ